# የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ

## ትምህርት ስድስት

## ድነት

# The Apostles' Creed

## Lesson six

## Salvation

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ይቅርታ**

የኀጢአት ችግር

    የኀጢአት ትርጉም

    የኀጢአት መነሻ

    የኀጢአት ጦስ

መለኮታዊ ጸጋ

    አብ

    ወልድ

    መንፈስ ቅዱስ

ግለሰባዊ ኃላፊነት

    ሁኔታ

    መንገድ

3. **ትንሣኤ**

መርገም

ወንጌል

    ብሉይ ኪዳን

    አዲስ ኪዳን

    የኢየሱስ ትንሣኤ

መቤዠት

    አሁን የምንኖርበት ሕይወት

    የመካከለኛው ዘመን ሁኔታ

    አዲስ ሕይወት

4. **የዘላለም ሕይወት**

ወቅት

ብርቅነት

ስፍራ

5. **ማጠቃለያ**

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

# 1. መግቢያ

እነዚህን ትምህርቶች በተመለከትንበት ጊዜ ሁሉ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የተዘጋጀው ቀደምት ክርስቲያኖች በሚጠመቁ ወቅት የእምነት አቋማቸውን በአጭሩ እንዲገልጡበት ዒላማ ተደርጎ እንደነበረ ጠቅሰናል፡፡ በዚያ አውድ መሠረት፣ ለአብዛኞቹ፣ በጋለ ስሜት የሚያስተጋቡት የሐይማኖት መግለጫው የእምነት አንቀጽ ስለ ግል ድነታቸው የሚናገረው ሊሆን እንደሚችል በቀላሉ መገመት እንችላለን፡፡

ለእኛስ ቢሆን ነገሩ እውነት አይደለምን? ታላቁን አምላካችንን እግዚአብሔር አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን እንወዳለን፡፡ እርሱ የመሠረታትንም ቤተ ክርስቲያን ትልቅ ዋጋ እንሰጣታለን፡፡ ለእኛ ታለቁ ደስታችን ግን ድነት ያገኘንበት መልካሙ የምሥራች ነው፡፡ በአሁንም ሆነ በሚመጣው ዓለም፣ እግዚአብሔር የሚወድደን መሆኑ፣ ኀጢአታችንን ይቅር ማለቱ፣ ለእኛም አስደናቂ የሆነ ፍጻሜ ያዘጋጀልን መሆኑን በማረጋገጣችን እጅግ ደስ ይለናል፡፡

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ላይ ከምንነጋገርባቸው ርዕሶች ይህ ስድስተኛው ትምህርት ነው፣ ርዕሱንም “ድነት” ብለን ሰይመነዋል፡፡ በዚህም ትምህርት፣ በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ የኀጢአት ይቅርታ እና የዘላለም ሕይወት ያገኘንበትን የምሥራች የሚያረጋግጠውን የእምነት አንቀፅ እንመለከታለን፡፡

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፣ “ድነት” የሚለው ቃል በበርካታ መንገዶች በክርስቶስ ያገኘነው መዳን ያሉትን ልዩ ልዩ ገፅታዎች ለማመልከት በአገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ የዘመናችን ክርስቲያኖች “ድነት” የሚለውን ቃል ስንጠቀም፣ ክርስቶስ በቤዝዎታዊ ሞቱ ለእኛ ያስገኛቸውን በረከቶች ሁሉ መቀበላችንን፣ ማለትም ዳግም መወለድንና ከእግዚአብሔር መታረቃችንን መነሻ በማድረግ፣ በመቀደስና በአዲሲቱ ሰማይና በአዲሲቱ ምድርም የሚጠብቀንን ክብር በማመልከት በሕይወታችን ዘመን ሁሉ የሚከናወኑትን ተግባራት በልቡናችን ይዘን ነው፡፡

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ስለዚህ የመዳን ጉዳይ የሚናገረው እንዲህ ሲል ነው፡

*በኀጢአት ስርየት፣*
*በሥጋ ትንሣኤ፣*
*እና በዘላለም ሕይወት*
*አምናለሁ፡፡*

ይቅርታ፣ ትንሣኤና የዘላላም ሕይወት የሚሉት እነዚህ ሦስት ሃሳቦች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መዳናችን የሚሰጠውን መግለጫ በዝርዝር አልያዙም፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እያንዳንዱን አማኝ ሲያድን ያከናወናቸውን ተግባራት ውስን ገፅታዎች  በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ውስጥ በአጭሩ ያስቀመጡ ቀደምት አንቀፆች ናቸው፡፡

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ላይ ስለ ድነት የምናደርገው ውይይት እነዚህ የመዳናችንን አድማሶች ይዳስሳል፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ኀጢአት ይቅርታ እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ የሥጋን ትንሣኤ አስተምህሮ እንዳስሳለን፡፡ ሦስተኛ፣ የዘላለምን ሕይወት ተፈጥሮ እንመለከታለን፡፡ እስኪ የተለመደውን የኀጢአትን ይቅርታ ርዕሰ ጉዳይ አስቀድመን እንመልከት፡፡

# 2. ይቅርታ

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ስለ ይቅርታ ሲናገር ማለት የፈለገውን ለመረዳት፣ ተዛማጅ የሆኑ ሦስት ጉዳዮችን እንነካካን፡፡ እነርሱም፡- አንደኛ፣ ይቅርታን አስፈላጊ ያደረገው የኀጢአት ችግር፤ ሁለተኛ፣ ይቅርታ እንዲገኝ ያስቻለውን መለኮታዊ ፀጋ፤ ሦስተኛ ደግሞ፣ ይቅርታን ለመቀበል ልናከናውናቸው የሚገቡንን፣ ግለሰባዊ ሃላፊነቶቻችንን እንዳስሳለን፡፡ አስቀድመን የኀጢአትን ችግር እንመለከታለን፡፡

# የኀጢአት ችግር

መጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ከሞተባቸው ዋና ምክንያቶች አንዱ በእኛ ኃጢአት ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ነው፡፡ ኃጢአት እኛን ከእግዚአብሔር በረከት ለየን፣ በእርሱም ፍርድ ስር እንድንወድቅ አደረገን፡፡ ስለዚህም በራሳችን ከዚህ ችግር ማምለጥ የምንችልበት ምንም መንገድ የለም፡፡ የኃጢአት ችግር ብለን ስንናገር ማለት የፈለግነው ይህንን ነው፡፡ ኃጢአት በኩነኔ ስር ጥሎናል፡፡ ከክርስቶስም በስተቀር፣ ራሳችንን ከኃጢአት ወይንም በኃጢአት ምክንያት ከሚመጣ ፍዳ ማስመለጥ የምንችልበት መንገድ የለንም፡፡

ስለ ኃጢአት ችግር ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያስተምሩንን ነገር በሦስት ክፍል ከፍለን እንመረምራለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ስለ ኃጢአት መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ፍቺ እናቀርባለን፡፡ ሁለተኛ በሰው ዘር ውስጥ ስለሚገኘው የኃጢአት ምንጭ እንነጋገራለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ኃጢአትን ተከትሎ ስለሚመጣው ፍዳ እንመለከታለን፡፡ እስኪ ስለ ኃጢአት ፍቺ በመነጋገር እንጀምር፡፡

# የኃጢአት ትርጉም

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኃጢአት በተለያየ መንገድ ይናገራል፡፡ ሕገወጥነት፣ አመፅ፣ መተላለፍ፣ በደል፣ ክፋት፣ ድንበር መጣስ፣ እና ሌሎችም በርካታ የሆኑ ኃጢአት የሞላባቸውን ድርጊቶች የሚገልጡ ቃላትን ይጠቀማል፡፡ እነዚህም ቃላት እያንዳንዳቸው ስለ ኃጢአት ያለንን ግንዛቤ ያዳብራሉ፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት ምስጢራዊ በሆነ መንገድ ስለ ኃጢአት ሲናገሩ ማለትም ስለ ኃጢአት የራሳቸውን ትርጉም ሲሰጡ፣ ከሁሉም ይልቅ አንድ ቃል ጎልቶ ይወጣል፣ ያም ሕገወጥነት (ሕግ አልባነት) የሚለው ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት መሠረት፣ ኃጢአት በመሠረቱ የእግዚአብሔርን ሕግ መተላለፍ ነው፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 4 ላይ እንደተናገረው፡

> ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል፥ ኃጢአትም ዓመፅ ነው።
> (1ዮሐ 3፥4)

ኃጢአት ሕግን መተላለፍ መሆኑን የሚያመለክቱ እንደ ሮሜ ምዕራፍ 7 ከቁጥር 9 እስከ 25፤ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ቁጥር 56 ያሉ ምንባቦችም አሉ፡፡ ይህ የኃጢአት መሠረታዊ ሃሳብ በበርካታ የተለያዩ ነገረ-መለኮታዊ ትውፊቶችም ውስጥ ይንፀባረቃል፡፡

አንድ ምሳሌ ብንወስድ፣ የዌስት ሚኒስትሩ አጭር የእምነት አንቀፅ (ካቴኪዝም) ጥያቄና መልስ ቁጥር 14 የሚናገረውን አድምጡ፡

> ኃጢአት ምንድን ነው?

> ካቴኪዝሙ እንዲህ ሲል መልስ ይሰጣል፡

> ኃጢአት የእግዚአብሔርን ሕግ ለመፈፀም አለመፈለግ፣ ወይንም መተላለፍ ነው፡፡

የእምነት አንቀፁ የሚሰጠው መልስ የአግዚአብሔር ሕግ የሚጣስባቸውን ሁለት መንገዶች ይገልፃል፡ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመፈፀም አለመፈለግ እና ሕግን መተላለፍ ናቸው፡፡

በአንድ በኩል፣ የእግዚአብሔርን ሕግ ለመፈፀም አለመፈለግ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚያዝዙትን አለመፈፀም ነው፡፡ ይህም ያለማድረግ ኃጢአት በመባል በተደጋጋሚ ይታወቃል ምክንያቱም ልናደርግ የሚገባንን አናደርግም ወይም ቸል እንላለን፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ ሕግን መተላለፍ ደግሞ ቅዱሳት መጻሕፍት የሚከለክሉትን ማድረግ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የሕግ ጥሰት የማድረግ ኃጢአት ይባላል ምክንያቱም በሃሳብ፣ በስሜት ወይንም ቅዱሳት መጻሕፍት የሚከለክሉትን አንድ ነገር በማድረግ ኃጢአት እንሠራለን፡፡

እንግዲህ አሁን፣ የእግዚአብሔርን ሕግ ኃጢአትን የሚገልጥ ልኬት አድርገን ስንነጋገር፣ የእግዚአብሔር ሕግ በመላምት ወይንም በጭፍን የሚበይን አለመሆኑን ማመልከት አስፈላጊ ነው፡፡ በተቃራኒው ግን፣ ሕግ የእግዚአብሔር ፍፁማዊ ባህርይ ነፀብራቅ ነው፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 7 ቁጥር 12 ጳውሎስ ሕግን የገለጠበትን መንገድ አድምጡ፡

> ስለዚህ ሕጉ ቅዱስ ነው ትዕዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት። (ሮሜ 7፥12)

በዚህ ስፍራ ጳውሎስ እንደተናገረው፣ የእግዚአብሔር ሕግጋት ልክ እንደ ራሱ እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ፣ ጻድቅና መልካሞች ናቸው፡፡ የእግዚአብሔር ትዕዛዛት ዘወትር ከባህርዩ ጋር ስምም ናቸው፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት እግዚአብሔርን የምንወድድ ከሆነ፣ ሕግጋቱንም እንደምንጠብቅ የሚያስተምሩት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ እግዚአብሔርን የምንወድድ ከሆነ፣ እግዚአብሔርን የሚገልጡ ነገሮችንም፣ ማለትም እንደ እርሱ ሕግጋት የመሳሰሉትን እንወድዳለን፡፡ ይህንንም በዘዳግም ምዕራፍ 5 ቁጥር 10 እና ምዕራፍ 6 ቁጥር 5 እና 6፤ ማቴዎስ ምዕራፍ 22 ከቁጥር 37 እስከ 40፤ ዮሐንስ ምዕራፍ 14 ከቁጥር 15 እስከ 24 እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች እናገኛለን፡፡ ዮሐንስ በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 3 ላይ የፃፈውን አድምጡ፡

> ትዕዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነውና፤ ትዕዛዛቱም ከባዶች አይደሉም። (1ዮሐ 5፥3)

የእግዚአብሔር ፍቅር ለእርሱ ሕግጋት ባለን መታዘዝ ይገለፃል፡፡ ስለዚህ፣ የእርሱን ሕግ ስንተላለፍ፣ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር በተግባር አንገልጥም ማለት ነው፡፡ ስለዚህም፣ እንበድላለን፡፡

*በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ እግዚአብሔርን በመውደድና በመታዘዝ መካከል ጥብቅ ግንኙነት አለ፡፡ እኔ እንደማስበው ግልፅ ማድረግ የሚገባን የመጀመሪያው ነገር እግዚአብሔርን እንዲያው እወደዋለሁ ማለት ብቻውን እግዚአብሔርን እንደንወድደው የተሰጠንን ትዕዛዝ ማሟላት አለመሆኑን ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ "ብትወዱኝስ"፣ ወይንም ኢየሱስ "ብትወዱኝስ ትዕዛዜን ጠብቁ" ካለ፣ ተግባር ተኮር፣ በባርነት መንፈስ የሚደረግና ብልቡና ፍቅር የሌለበት ጉድ ጉድ አይቶብናል ማለት ነው፡፡ ፍቅር ካለ፣ በእግዚአብሔር ደስ በመሰኘት ላይ መሠረቱን ያጠበቀ ራስን የመስጠት ፈቃደኝነት ካለ ግን፣ የዚያ ነፀብራቅ የሆነው ነገር ፍፁም ተፈጥሯዊ በሆነና ዋጋ ባለው መንገድ ይገለጣል፣ የምትወዱትንና በእርሱም ደስ የምትሰኙበትን እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ለመታዘዝም ዝግጁዎች ትሆናላችሁ፡፡ ይህም የተመሠረተው "የእግዚአብሔር መንገድ" ይህ ነው በሚለው አቋም ላይ ሲሆን አስተማማኝና እንደ እርሱም ባህርይ ለእናንተ ለመልካም የሚሠራ ነው፡፡ [ዶ/ር ግሌይን ስኮርጂ]*

የምናደርገውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ባለን ፍቅር የማናደርግ ከሆነ፣ በእርሱ ላይ በማመፅ ኃጢአትን እናደርጋለን፣ ሕግጋቱን እንተላለፋለን፣ ክፉ እንሠራለን፣ ከመስመር እንወጣለን፣ የእርሱንም ቅዱስና ጻድቅ ባሕርይ እናሳዝናለን፡፡ የእግዚአብሔር ፍቅር ሲያነሳሳን ግን፣ የእርሱን መሻቶችና ግዴታዎች ከእኛ በላይ እናስቀምጣቸዋለን፡፡ በውጤቱም፣ በርካታ ኃጢአቶችንና በሕይወታችንም የሚያስከትሉትንም አሰቃቂ መዘዝ እናስወግዳለን፡፡

ይህንን የእግዚአብሔርን ሕግ የመተላለፍ የኃጢአትን ፍቺ በልቡናችን ይዘን፣ ኃጢአት በሰው ዘር ውስጥ የገባበትን ምንጩን እንመለከታለን፡፡

## የኃጢአት ምንጭ

አብዛኞቻችን በዘፍጥረት ምዕራፍ ሦስት የተመዘገበውንና የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን አዳምና ሔዋን ከተከለከለችውና መልካምና ክፉን ከምታስታውቀው ዛፍ በመብላት በእግዚአብሔር ላይ ማመፃቸውን እናውቃለን፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ አተያይ አንፃር ይህ ድርጊት የብቻቸው ድርጊት ሆኖ አልቀረም፡፡ ጠቅላላው የሰው ዘር በደለኛ እንዲሆን አደረገው፡፡ በበደልም የረከሰ አደረገው፡፡ የነገረ-መለኮት ምሁራኑም ይህንን ክስተት የሰው ዘር በኃጢአት መውደቅ ወይንም በቀላሉ ውድቀት በማለት ይጠቅሱታል፡፡

ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ከቁጥር 26 እስከ 31 እንደሚነግረን፣ እግዚአብሔር የሰውን ዘር ሲፈጥር መልካም እንደነበርን እንረዳለን፡፡ በዚህ ጉዳይ፣ “መልካም” ማለት እኛ እግዚአብሔር እንድንሆን የሚፈልገውን ዓይነት ሰዎች ነበርን ማለት ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹም ወላጆቻችን የእግዚአብሔር ንፁህ ግብረገባዊ አምሳሎች፣ እግዚአብሔር የፈጠረውንም ዓለም በመሙላትና በመግዛት ያገለግሉት ዘንድ የተጣመሩ ነበሩ፡፡

በሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 12 ጳውሎስ እንዳመለከተው፣ ከውድቀት በፊት ኃጢአት በሰው ዘር ውስጥ አልገባም ነበር፡፡ ኃጢአትን ፈፅሞ አላደረግንም፣ ወደ ኃጢአትም አናዘነብልም ነበር፣ በኃጢአትም የረከሰን አልነበርንም ደግሞም የኃጢአት ማደሪያም አልነበርንም፡፡

በዚህ ኃጢአት አልባ ሁኔታ ውስጥ እያለንም ቢሆን እንኳን፣ ኃጢአትን የማድረግ ዕድሉም ሆነ ችሎታው ግን ነበረን፡፡ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ፈጥሮ በዔድን ገነት ውስጥ ሲያስቀምጣቸው፣ በርካታ ነገሮችን ገልጦላቸው ነበር፡፡ እግዚአብሔርን ለማገልገል ፈቃደኛ መሆናቸው የሚፈተሽበት አንድ ትዕዛዝ ግን ብዙም ሳይቆይ በግልፅ ተነግሯቸው ነበር፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁር 16 እና 17 ፣ አዳምና ሔዋን በገነት ካለው ዛፍ ሁሉ እንዲበሉ ግን መልካምና ክፉን ከምታስታውቀው ዛፍ እንዳይበሉ እግዚአብሔር እንዳዘዛቸው እናነባለን፡፡ አዳምና ሔዋን ይህንን ሕግ በመተላለፍ ኃጢአትን የመሥራቱ ፈተና ከፊታቸው ተጋረጠ፡፡

አሳዛኝ በሆነ መንገድ፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ከቁጥር 1 እስከ 6 እንደምናገኘው፣ ከተከለከለው ዛፍ እንድትበላ እባቡ ሔዋንን አታለላት፡፡ ሔዋን ከፍሬው ጥቂቱን እንዲበላ ለአዳም ሰጠችው፣ አዳምም በላ፡፡ አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን የጽድቅ ሕግ ተላለፉ ወድደውም ኃጢአት ማድረግን መረጡ፡፡ ራዕይ ምዕራፍ 12 ቁጥር 9 እንደሚያሳየን እባቡ ሰይጣን ነበር፣ 1ኛጢሞቴዎስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 14 እንደሚያመለክተን የተታለለችው ሔዋን ነበረች፡፡ ግን የሰይጣን ፈተናም ሆነ የሔዋን መታለል የመጀመሪያ ወላጆቻችንን ኃጢአት እንዳይቆጠርባቸው አላደረጉም፡፡ ሁለቱም ከመልካም ይልቅ ክፉውን በመምረጥ በደለኞች ሆኑ፡፡

በእነዚህ ክስተቶችም በመሠረቱ ኃጢአት የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማለትም ህጉን የመተላለፍ ጉዳይ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ ከእግዚአብሔር የተገለጠ ህግ በተላለፈ መንገድ ስናስብ፣ ስንናገር ወይንም አንድ ድርጊት ስንፈፅም ከመልካሙ ይልቅ ክፉውን መምረጣችን ነው፡፡ ምንም እንኳን ኃጢአትን ለማድረግ የተታለልን ወይንም የተሞኘን ብንሆንም፣ በሠራነው ሥራ እግዚአብሔር ተጠያቂዎች ያደርገናል፡፡ በልባችን የእግዚአብሔርን ቃል መሰወር የሚገባን ለዚህ ነው፡፡ ስለምናውቅ ብቻ ሳይሆን ስለምንወድደውም ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግጋት

ስናውቅ፣ ኃጢአትን ለይተን እንድናውቅ ያደርገናል ስለዚህም አንታለልም፡፡ የአግዚአብሔርንም ሕግ ስንወድድ፣ እርሱን መታዘዝን ምርጫችን ለማድረግ የበለጠ ይቀለናል፡፡

የኃጢአትን ፍቺና ምንጭ ከተረዳን፣ የኃጢአትን መዘዞች ደግሞ እንለከታለን፡፡

# የኃጢአት መዘዞች

አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ካደረጉ በኋላ እግዚአብሔር መላውን የሰው ዘር እንደረገመና እንደፈረደበት ቅዱሳት መጻሕፍት ያመለክቱናል፡፡ ይህም እርግማን የማንታቸውን የትኛውንም ነገር አናጋው፡፡ ወዲያውኑም በቅዱሳት መጻሕፍት በየስፍራው እንደተነገረው መንፈሳዊ ሞትን አስከተለ፡፡ ይህንንም ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 24 እና 25፣ ኤፌሶን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1 እስከ 5፣ ቆላስያስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 13 እና 14 በመሳሰሉት ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ በተጨማሪም በማንነታችን ላይ መርከስን አስከትሏል፣ ይህም በአካልም በነፍስም መሆኑን በኤርምያስ ምዕራፍ 17 ቁጥር 9 እና ሮሜ ምዕራፍ 7 ከቁጥር 18 እስከ ምዕራፍ 8 ቁጥር 11 ባሉት ውስጥ እንመለከታለን፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 19 እና ሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 12 እንደምንመለከተውም ለአካላዊ ሞት ዳረገን፡፡ በመጨረሻ፣ ከማቴዎስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 29 እና 30 እንደምንረዳው ኃጢአት የሰው ዘር በሲዖል ውስጥ በእግዚአብሔር ፍርድ ስር ለዘላለም እንዲሰቃይ አድርጎታል፡፡

እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ከ1834 እስከ 1892 የኖረው ዕውቁ መጋቢ ቻርለስ ስፐርጀን፣ The Curse Removed በተሰኘው ስብከቱ፣ በአዳምና በሔዋን ላይ ስለወደቀው የእግዚአብሔር ፍርድ ተናግሯል፡፡ እስኪ ምን እንደተናገረ አድምጡ፡

> *መርገሙ ምን ምን ነገር አስከትሎ ነበር? ሞትን አስከትሎ ነበር፣ ያም ሞት የዚህ የአካላችን ሞት ነበር.. መንፈሳዊ ሞትንም አስከትሎ ነበር፣ ያም ሞት አዳም የነበረው የውስጣዊ ሕይወት ሞት ነው፡፡ አሁን ከእኛ የተለየውና በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እንደገና ተመልሶ ሕያው ሊሆን የሚችል የመንፈሱ ሕይወት ነው፡፡ ከሁሉ የመጨረሻውና ከሁሉ የከፋው፣ "ሲዖል" በተሰኘው አስደንጋጭና አሰቃቂ ቃል ውስጥ በአንድነት የሚከማቸው ዘላለማዊ ሞት ነው፡፡ [ቻርለስ ስፐርጀን]*

ከዚህ የከፋው ደግሞ፣ የአዳምና የሔዋን ኃጢአት መዘዝ ወደ ሰው ዘር ሁሉ ማለትም በተፈጥሯዊ ውልደት ከእነርሱ በሚወጣው ትውልዳቸው ሁሉ ላይ ተስፋፋ፡፡ የኃጢአትን አለም

አቀፋዊ ስፋት 1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 8 ቁጥር 46፤ ሮሜ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 9 እስከ 12፤ ገላትያ ምዕራፍ 3 ቁጥር 22 እና ኤፌሶን ምዕራፍ 2 ቁጥር 3 ላይ እንመለከተዋለን፡፡ እስኪ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 12 እና 19 ላይ ስለ አዳም ኃጢአት የተናገረውን አድምጡ፡

> ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ … በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ። (ሮሜ 5፥12፡19)

ቀደም ባለው ትምህርት እንደተመለከትነው፣ አዳም የሰው ዘር ሁሉ የቃል ኪዳን ራስ ነበር፡፡ ጳውሎስም እንዳስተማረው፣ በዚህም ምክንያት የአዳም ኃጢአት በዘሮቹ ሁሉ ላይ ተቆጠረባቸው፡፡ በውጤቱም፣ ከፍጥረታችን ኃጢአተኞች ሆንን፡፡ ወደ ዓለምም መንፈሳዊ ሙታን ሆነን፣ ለስቃይና ለመከራ ተዳርገን እና በአካላዊ ሞት የምንሞት ሆነን መጣን፡፡

> *ኃጢአት የሚያስከትለውን ጣጣ ሙሉ በሙሉ መረዳት አንችልም፡፡ የእኛ ኃጢአት ግን በፈጣሪያችን ላይ ማመፅ ነው፡፡ የእርሱን ክብር ማቃለል፣ ሕግጋቱንም ማፍረስ፣ ከእርሱም ክብር መጉደል ነው፡፡ በየትኛውም መንገድ ብንመለከተው ራሳችንን የእግዚአብሔር ጠላቶች አድርገን ማሰለፍ ነው፡፡ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት አውኮታል ምክንያቱም እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና፡፡ እርሱ ኃጢአትን ሊመለከት አይችልም፡፡ ከቅድስናውም የተነሳ፣ በኃጢአት ላይ ቁጣውን ያፈስሳል፡፡ እንግዲያው፣ የሰውን ዘር ኃጢአተኝነት ስንመለከት፣ ስለ ችግራችን ልንረዳው የሚገባንን ነገር ሁሉ ያዘለ ነገር ነው፡፡ ስለ ማንነታችንም ጭምር ልናውቀው የሚገባንን ነገር ሁሉ ያዘለ ነገር ነው፡፡ ኃጢአት ማለት፣ በመስታወት የምንመለከተውንና ነን ብለን የምናውቀውን ማንነታችንን እንድንረዳው የሚያግዘን አራት ፊደላት ብቻ ያሉት አጭር ስነ-አዕምሮ ነው፡፡ በተጨማሪም ከዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ራሳችንን ማውጣትና መታደግ የምንችልበት ምንም መንገድ የሌለን መሆኑንም የሚያሳስበን ነው፡፡ ይህንን ማድረግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፣ ይህንንም በክርስቶስ ፈፅሞታል፡፡ [ዶ/ር አር. አልበርት ሞህለር፣ ትንሹ]*

የኃጢአት መዘዝ በእውነት አደገኛ ነው፡፡ የሰው ዘር በጠቅላላ ፈፅሞ ጠፍቷል ተኮንኗልም፡፡ ራሳችንን ማዳን የምንችልበት ምንም መንገድ የለንም፡፡ በእግዚአብሔር ፍርድ ስር መውደቅም ልናመልጠው የማንችል ዘላቂ ዕጣ ፈንታችን ሆኗል፡፡ የእርሱን ሞገስ መልሰን የራሳችን ማድረግ

የምንችልበት መንገድ የለንም፣ ወይንም ለኃጢአታችን ካሳ መክፈል አንችልም፡፡ ከእግዚአብሔር የማያልቅበት ይቅርታ በስተቀር፣ መዳን የምንችልበት ተስፋ ጨርሶውኑ የለም፡፡

የኃጢአትን ችግር ከተመለከትን፣ በእግዚአብሔር መለኮታዊ ጸጋ ምክንያት ስለተገኘው የኃጢአት ይቅርታ ወደ ምንነጋገርበት ርዕስ እንሸጋገራለን፡፡

## መለኮታዊ ጸጋ

ከምህረቱ የተነሳ፣ የሰው ዘር በኃጢአት እርግማን ስር እንዲቆይ እግዚአብሔር አልፈቀደም፡፡ አሁንም ቢሆን የሰው ዘር ምድርን እንዲሞላና እንዲገዛ፣ ለእርሱ መገኘትም የምትመጥን መንግሥት ሆና እንድትለወጥም አቅዷል፡፡ ስለዚህም፣ የኃጢአትን ችግር ይፈታ ዘንድ የሚቤዠውን ላከ፡፡ ያም ቤዛ ልጁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

እንደ አዳኝ፣ ኢየሱስ ከበደልና ከእርኩሰታችን አዳነን፤ ከራሱም ጋር አስታረቀን፣ ዓለምንም የእርሱ ምድራዊ መንግሥት ሆና እንድትለወጥ ማድረግ የምንችልበትን አቅም መለሰልን፡፡ የእግዚአብሔር ዕቅድ ግን ራሳችንን ለማዳን በሚደረግ በሰው ዘር ከንቱ መፍጨርጨር ላይ አይደገፍም፡፡ የሚደገፈው ወደር በማይገኝለት ወኪላችን፤ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በተቀበልነው በእግዚአብሔር ጸጋ፣ የይገባኛል ጥያቄ በማይቀርብበት ሞገሱ ላይ ብቻ ነው፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 3 ቁጥር 23 እና 24 ላይ እንደምንመለከተው ማለት ነው፡

> ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤
> በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው
> ይጸድቃሉ።
> (ሮሜ 3፥23-24)

እንደ መለኮታዊ የጸጋ ሥራ፣ ይቅርታ የስላሴን ሦስቱንም አካላት፣ አብን፣ ወልድንና መንፈስ ቅዱስን ያካትታል፡፡ በእግዚአብሔር አብም ይጀምራል፡፡

## አብ

*ድነት በመሠረቱ ሥሉሳዊ ነው፡፡ አብ የቀየሰው፣ ወልድ የፈፀመው፣ መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሕይወት የሚተገብረው ነው፡፡ ስለ አብና ወልድ ግንኙነት ስናስብ፣ ስለ አብ፣ ስለ ወልድና ስለ መንፈስ ቅዱስ ልናስብ ይገባል ምክንያቱም ሦስቱም በእኛ የመዳን ዕቅድ ውስጥ*

*ተሳትፈዋልና፡፡ ሦስቱም አካላት በፀጋ፣ በፍቅርና በምህረት ተገልጠዋል ደግሞም የእግዚአብሔር የጽድቁ ቁጣና ፍርድ እንዳያርፍብንም ከልለውናል፡፡ እንግዲያው አብ ቢቀይሰውም፣ ከወልድና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ ግን አላከናወነውም፡፡ [ዶ/ር ስቴፈን ዌሉም]*

ይቅርታ የተጀመረው በአብ ነው ምክንያቱም ያቀደው እርሱ ነውና፡፡ አዲስ ኪዳን በውል እንደሚያስተምረን አብ አንድያ ልጁን ቤዛ አድርጎ ወደ ዓለም ልኮታል፡፡ ይህንንም በዮሐንስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 16 እስከ 18፤ የሐሥ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 34 እስከ 36 እና በዕብ ምዕራፍ 3 ቁጥር 1 እና 2 ላይ እንመለከታለን፡፡

አዲስ ኪዳን በተጨማሪም እንደሚያስተምረን ኢየሱስ ለህዝቡ ቤዛ ሊሆን የሚያስችለውን ኃይል ኢየሱስ እንዲለብስ ደግሞም ኢየሱስ በመስቀል ላይ የከፈለው መስዋዕትነት የኃጢአት ዕዳ ክፍያ እንዲሆን አብ ፈቀደ፡፡ ስለዚህ የአብ ድርሻ ዮሐንስ ምዕራፍ 10 ከቁጥር 14 እስከ 18፤ ቆላስይስ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 18 እስከ 20 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 2 ቁጥር 10 በመሳሰሉት ምንባቦች ውስጥ እናነባለን፡፡

በመሠረቱ፣ ሮሜ ምዕራፍ 3 ቁጥር 25 እንደሚናገረው ኢየሱስን መስዋዕት አድርጎ የሰጠን አብ ነው፡፡ ጳውሎስ በዚያ ስፍራ የጻፈውን አድምጡ፡

> እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤ (ሮሜ 3፥25)

አብ ታላቁ የድነት አርክቴክት ነው፡፡ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለንና ሊባርከን የእርሱ ጸጋ የሞላበት ዕቅዱና ምህረትን የተሞላ መሻቱ ነው፡፡ ድነት እንዲገኝና የተረጋገጠም እንዲሆን ያደረገው የእርሱ ሥልጣን ነው፡፡

*ኢየሱስ በመስቀል ላይ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ያለውን ቁጣ እንዲበርድ አደረገ የሚለው ሃሳብ ኢየሱስ አፍቃሪ አብ ግን ፍቅር የጎደለው አስመስሎ የማቅረቡ አዝማሚያ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ የማስተሰረይ ሥራ ውስጥ የተከናወነው ተግባር ፈጽሞ ተፃራሪና በቀላሉ የማይታይ ግድፈት ነው፡፡ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሠራው ሥራ አግዚአብሔር ለሕዝቡ የነበረው ቀደምት ፍቅር መግለጫ ነው፡፡ የኢየሱስ ወደ ዓለም መምጣትና መስቀልን መሸከሙ የአብ ፍቅር ውጤት እንደሆነ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ምን ያህል በተደጋጋሚ አፅንኦት እንደተሰጠው አስቡ፡፡ በክርስትና ሕይወት መጀመሪያ ላይ አብዛኛዎቻችን በቃላችን ያጠናነው ጥቅስ*

*ዮሐንስ 3፥16 እንዳጠቃለለው "... እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና " በዚህ ጥቅስ ትኩረት የተሰጠበት የማን ፍቅር ነው? ይህንን ስል በምንም መንገድ የኢየሱስን ፍቅር ከውስጡ ማውጣት ፈልጌ አይደለም፣ በምንባቡ ውስጥ ትኩረት የተሰጠው አንድያ ልጁን የሰጠው የሰማያዊው አባታችን የአብ ፍቅር ነው ለማለት ነው፡፡ [ዶ/ር ጄ. ሊዮን ዱንካን]*

# ወልድ

የእኛን ይቅር መባል የፈፀመው መለኮታዊ ጸጋ ቤዛችን የሆነውን ወልድንም ይጨምራል፡፡

የአብ ተስፋ ይፈፀም ዘንድ፣ ወልድ ወደ ዓለም ተላከ፣ እርሱም የሰውን ዘር ኃጢአት ያስተሰርይ ዘንድ ኢየሱስ የተባለው ትስጉት፣ ለረጅም ዘመን ሲጠበቅ የነበረው መሲህ ሆኖ መጣ፡፡ ይህንንም ትምህርት ሮሜ ምዕራፍ 3 ቁጥር 25 እና 26፤ ዕብራውያን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 14 እስከ 17 እና ምዕራፍ 10 ከቁጥር 5 እስከ 10 ባሉ በርካታ ስፍራዎች ውስጥ እናገኘዋለን፡፡

ኢየሱስ በኃጢአተኞች ምትክ በመስቀል ላይ በመሞት ኃጢአትን አስተሰረየ፡፡ በበደላችን ምክንያት አይቀሬ የነበረውን መለኮታዊ እርግማን ተቀበለ፡፡ የእርሱም ፍፁም ፅድቅ ለእኛ ተቆጠረልን፣ ስለዚህም እኛ እንደ በደለኞች መቆጠራችን ቀረና እንደ ታዛዥ የእግዚአብሔር ልጆች ተቆጠርን፡፡ ይህ መሪ ቃል ከታየባቸው ቦታዎች መካከል ጥቂቶቹን ብንጠቅስ፣ በዮሐንስ ምዕራፍ 10 ከቁጥር 14 እስከ 18፤ ገላትያ ምዕራፍ 2 ቁጥር 20፤ 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 21 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 10 ከቁጥር 9 እስከ 14 ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕራፍ 1 ቁጥር 7 እንደ ጻፈው፡

> በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም የበደላችን ስርየት። (ኤፌ 1፥7)

በደሎቻችን ይቅር የተባሉት እግዚአብሔር ቸል ስላላቸው ሳይሆን፣ በክርስቶስ ስለቀጣቸው ነው፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት በመዳናችን ረገድ ይህንን የመሰለ መተማመን እንዲኖረን የሚያበረታቱን ለዚህ ነው ፡፡

በአብና በወልድ እነዚህን መሳይ *ሥራዎች* ከመደገፉ ባሻገር፣ ያገኘነው ይቅርታ የመንፈስ ቅዱስም መለኮታዊ ጸጋ ውጤትም ነው፡፡

# መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስ ይቅር መባላችንን በሕይወታችን በተግባር የሚገልጥ የሥላሴ አካል ነው፡፡ አብ አቀደ ወልድ ደግሞ በደላችንን አስተሰረየ፡ መንፈስ ቅዱስ የራሱን ድርሻ ካላተወጣ ግን ኃጢአታችን ይቅር አይባልም፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ማመን ስንመጣ፣ አስከዚያች ቅፅበት ድረስ ያከናወናቸውን ኃጢአቶች ሁሉ ይቅር በማለት መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቀናል፡፡ በተጨማሪም ኢየሱስ በዮሐንስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 5 እስከ 8 እንደተናገረው፣ መንፈሳችን ዳግም እንዲወለድ በማድረግ አዲስ መንፈሳዊ ሕይወት ይሰጠናል፡፡ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 11 ቁጥር 18 ይህንን ልምምድ "ለሕይወት የሚሆን ንስሓ" በማለት ይገልጠዋል ምክንያቱም ዳግም መወለድና እምነት ዘወትር ስለበደላችን መፀፀትንና መናዘዝን ያካትታሉና ነው፡፡ ይህ ሃሳብ ለምሳሌ እንደ 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 11 በመሰለውና በሌሎችም በርካታ ምንባቦች ተረጋግጧል፡፡

መንፈስ ቅዱስ እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ ድረስ ይቅር መባላችንን የማፅናት ሥራውን ቀጥሏል፡፡ ወደ ዕለታዊ ንስሓ የሚመራን ለዘለቄታውም ይቅር መባላችንን በሕይወታችን የሚረጋገጥበትን እምነታችንን የሚያፀናልንም እርሱ ነው፡፡ ይህንንም እንደ ሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 1 እስከ 16 እና ገላትያ ምዕራፍ 5 ቁጥር 5 በመሳሰሉ ስፍራዎች እንመለከተዋለን፡፡ አንዱን ለምሳሌ ለማንሳት ይህል፣ ጳውሎስ በተሰሎንቄ ምዕራፍ 2 ቁጥር 13 የጻፈውንአድምጡ፡

> እኛ ግን፥ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፥ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኵራት መርጦአችኋልና፤ (2ኛ ተሰ 2፥13)

በዚህ ስፍራ፣ ጳውሎስ አማኞች የዳኑት እኛን ከኃጢአትና ከርኩሰት ባነፃን በመንፈስ ቅዱስ ሥራ መሆኑንና ያም ሥራ ይቅር መባላችንን በሕይወታችን ውስጥ የማፅናቱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፡፡ እኛ እውነትን ማመናችን ስንቀጥል፣ መንፈስ ቅዱስም ይቅር መባላችንን በሕይወታችን ማፅናቱን ይቀጥላል፡፡

አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ሁሉም የሚያድነውን ጸጋ በእኛ ሕይወት ውስጥ ይገልጣሉ፡፡ ይህም በእኛ ሕይወት ውስጥ ቢያንስ ሦስት አንድምታዎች አሉት፡፡ አንደኛ፣ ኃጢአትን

ስንፈፅምና በደላችንን ይቅር እንዲለንና ከመዳን ጋር የተያያዙ ነገሮችንም እንዲያደርግልን እግዚአብሔርን ስንለምን፣ ልመናችን በሦስቱም የሥላሴ አካላት ዘንድ እንዲታወቅ የማድረግ መብት አለን፡፡ ሁለተኛ፣ እነዚህን በረከቶችም ስንቀበል፣ ለእግዚአብሔር የስላሴ አካላት ሁሉ ምስጋናችንን ልናቀርብ ይገባል፡፡ ሦስተኛ፣ ሦስቱም የሥላሴ አካላት እንደሚወድዱንና መቤዠታችንንም እውን ለማድረግ የሚሠሩ መሆኑን በማወቅ በመዳናችን ታላቅ መተማመን ይኖረናል፡፡ አብ፣ወልድና መንፈስ ቅዱስ የኃጢአትን ችግር ለመፍታት ስለ እኛ በአንድነት ይሠራሉ፡፡

የኃጢአትን ይቅርታ ከኃጢአት ችግርና ከመለኮታዊ ጸጋ አንፃር ከተመለከትን፣ ይቀርታን አስመልክቶ የግለሰባዊ ሃላፊነት ድርሻ ምን እንደሆነ መመልከታችንን እንቀጥላለን፡፡

# ግለሰባዊ ሃላፊነት

እግዚአብሔር እንዲያው የሁሉንም ሰው ኃጢአት ይቅር እንደማይል ቅዱሳት መጻሕፍት በግልፅ ያስተምራሉ፡፡ አንዳንዶቹ ይቅር ተብለዋል፣ አንዳንዶቹ ግን አልተባሉም፡፡ ይህ ለምን እውነት ሆነ? ከሰብዓዊ አመለካከት አንፃር፣ ምክንያቱ የይቅርታ ሂደት በመደበኛነት የግለሰቡን ሃላፊነት የሚያካትት መሆኑ ነው፡፡ በጥቅል አነጋገር፣ ይህንን ሃላፊነታቸውን የተወጡ ሰዎች ይቅር ይባላሉ፣ ይህንን ሃላፊነት የሚሸሹ ግን ይቅር አይባሉም፡፡

በግለሰባዊ ሃላፊነት ላይ የምናደርገው ውይይት በሁለት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ አንደኛ፣ ቅዱሳት መጻሕፍት ለይቅርታ አስፈላጊ ናቸው ብለው ያስቀመጧቸውን ጥቂት ሁኔታዎች እንጠቅሳለን፡፡ ሁለተኛ ደግሞ፣ ይቅርታ የምንቀበልበትን መንገድ እንጠቅሳለን፡፡ እስኪ አስቀድመን ቅዱሳት መጻሕፍት ከይቅርታ ጋር ያዛመዷቸውን ሁኔታዎች እንመልከት፡፡

# ቅድመ ሁኔታዎች

ለይቅርታ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች እንዳሉ ቅዱሳት መጻሕፍት ይናገራሉ፡፡ በመጀመሪያ ለይቅርታ በእግዚአብሔር ማመን ቀዳሚ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፣ እምነት ባለ ብዙ ገፅታ ሃሳብ ነው፡፡ በዚህ አውድ ግን፣ በእግዚአብሔር ስለ ማመን ስንናገር፣ በልቡናችን ያስቀመጥነው፡

*ለእግዚአብሔር መለኮታዊ ሉዓላዊነት እውቅና መስጠት፣ ለእርሱም በታማኝነት ራስን መስጠት፣ ስለ ቤዛችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም ሲል ምህረትን እንደሚያደርግልን ማመንን ነው፡፡*

ምንም እንኳን ለዘመነኛው አድማጭ ነገሩ እንግዳ ቢመስልም፣ ይህንን መሳዩን እምነት ቅዱሳት መጻሕፍት "እግዚአብሔርን ከመፍራት" ጋር ያዛምዱታል፡፡

ለምሳሌ፣ መዝሙር 103 ከቁጥር 8 እስከ 13 የይቅርታን ቅድመ ሁኔታዊ ተፈጥሮ በዚህ መንገድ ይገልፀዋል፡

> እግዚአብሔር መሓሪና ይቅር ባይ ነው፥ ከቍጣ የራቀ ምሕረቱም የበዛ።
> ሁልጊዜም አይቀሥፍም፥ ለዘላለምም አይቈጣም።
> እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም፥ እንደ በደላችንም አልከፈለንም።
> ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥ እንዲሁ እግዚአብሔር ምሕረቱን
> በሚፈሩት ላይ አጠነከረ።
> ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፥ እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ።
> አባት ለልጆቹ እንደሚራራ እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል
> (መዝ 103፥8-13)

የእርሱን ይቅርታ የሚቀበሉትና መተላለፋቸውም የሚደመሰስላቸው፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩት መሆናቸውን ልብ ይሏል፡፡

ይኸው ተመሳሳይ ሃሳብ በመላው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል፡፡ ለአብነት፣ በ2ኛ ዜና ምዕራፍ 30 ከቁጥር 18 እስከ 19 ላይ፣ ልባቸውን ወደ እርሱ የሚያዘነብሉትን ጌታ ይቅር እንደሚላቸው እናነባለን፡፡ በማርቆስ ምእራፍ 4 ቁጥር 12 ላይም፣ ጌታን የሚያውቁና የሚረዱትም ለምህረት ወደ እርሱ የሚመለሱ መሆናቸውን ኢየሱስ አመልክቷል፡፡ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 26 ቁጥር 17 እና 18 ላይ፣ ይቅርታን የሚያገኙት ዐይኖቻቸው የጌታን ክብርና ኃይል ለመመልከት የተከፈቱላቸው መሆናቸውን ይናገራል፡፡

ለይቅርታ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የምናገኘው ሁለተኛ ቅድመ ሁኔታ ልበ ሰባራነት ነው፡፡ ሰባራነት፡

ስለ ሠራነው ኃጢአት በእውነት ማዘን፤ የአግዚአብሔርንም ሕግጋት በመተላለፋችን መፀፀት ነው፡፡

ስለተደረሰብን ወይንም ስለተቀጣን ማዘን ብቻ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ቅድመ ሁኔታዎች ቅዱስ ስለ መሆናቸው መስማማት፣ እርሱን ባለማክበራችንም በእውነት ከልብ መሰበር ነው፡፡

*መፀፀት ስንል፣ ማለት የፈለግነው፣ ስለ ኃጢአታችን እናንተና እኔ በደለኝነት ይሰማናል ማለታችን ነው፡፡ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ኃጢአትን ከፈጸመ በኋላ ስለ ሆነው ነገር አስባለሁ፡፡ እርግጥ ነው በቤርሳቤህ ላይ በደልን ፈጽሟል፣ በቤርሳቤህም ባል ላይ በደልን ፈጽሟል፡፡ በብሉይ ኪዳን ቤተክርስቲያንም ላይ በደልን ፈጽሟል፣ በዋናነት ግን "አንተን ብቻ በደልሁ፥ በፊትህም ክፉትን አደረግሁ፥" አለ፡፡ ከልቡ ስለ መፀፀቱ አንድ የምንረዳው ነገር አለ፡፡ እኔ እንደማስበው ዘመነኛው ቃል "ሰባራነት" የሚለው ነው፣ እናም እኛ ቃሉ፣ በመንፈሱ አማካይነት፣ በእግዚአብሔር ፊት ሊሰባብረን ይገባል፡፡ [ዶ/ር ዴሪክ ደብሊዩ ኤች ቶማስ]*

ለምሳሌ፣ በ2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 11፣ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ካመነዘረ በኋላ፣ የመፀፀት አዝማሚያ አላሳየም ነበር፣ እንዲያውም ማርገዟን ለመሸፈን ባሏ ያርዮ የሚሞትበትን መንገድ ቀይሷል፡፡ በቤርሳቤህ የእርግዝና ወራትና ልጁም እስከ ልጁም መወለድ ድረስ በድርጊቱ ምንም ሳያዝን ኖሯል፡፡ ከ2ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 12 እንደምንማረው ግን፣ ነቢዩ ናታን ዳዊትን ስለኃጢአቱ ፊት ለፊት ሲጋፈጠው እንመለከታለን፡፡ ዳዊት ወንጀል መፈፀሙን ያመነውና በጥልቅም ያዘነው ያን ጊዜ ነው፡፡ ከዚያም፣ በእውነተኛ የተሰበረ ልብና መንፈስ፣ የሃዘኑን ጥልቀትና መፀፀቱንም የሚገልጥበትን ታላቁን የንስኃ መዝሙሩን መዝሙር 51 ጻፈ፡፡ ዳዊት በመዝሙር 51 ቁጥር 6 እና 17 ላይ የተናገረውን አድምጡ፡

> እነሆ፥ እውነትን ወደድህ የማይታይ ስውር ጥበብን አስታወቅኸኝ።...የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፥ የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም። (መዝ 51፥6፣17)

የእግዚአብሔርን ይቅርታ ለመቀበል፣ ስለ ኃጢአቱ እግዚአብሔር ያለውን አመለካከት ሊጋራ እንደሚገባው ዳዊት ተረድቷል፡፡ የፈፀመውን ድርጊት ሊጠየፈውና በእውነትም ሊያዝን ይገባው ነበር፡፡

ከሰባራነት አንፃር ተመሳሳይ የሆነውን አጽንዖት ይቅርታን የሚያገኙ በውስጣቸው ሽንገላ የሌለባቸው መሆናቸው በተጠቀሰበት በመዝሙር ምዕራፍ 32 ቁጥር 1 እና 2 ላይ እናገኛለን፡፡ በኢሳያስ ምዕራፍ 55 ቁጥር 7፣ ኃጢአታቸውን የሚተዉ የእግዚአብሔርን ምህረት እንደሚቀበሉ ተጽፎ እናገኛለን፡፡ በኤርምያስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 3 ላይ ደግሞ፣ ስለ ኃጢአታቸው ልባቸው የደነደነ ግን ምህረትን እንደማያገኙ እንመለከታለን፡፡

*ልቡናችን በእግዚአብሔር ቅዱስነት ላይ እንዲያተኩር በማድረግ፣ የእውነተኛ ንስሓ እምብርት የሆነውን ፀፀት በተገቢው ደረጃ ልናከናውነው እንችላለን፡፡ ይህንንም እግዚአብሔር ከማይታዘዙ ህዝቦች ጋር ኅብረት እንደማያደርግ፣ አለመታዘዝን ግን እንደሚቀጣና ተላላፊዎችንም እንደሚበቀል ከዘፍጥረት እስከ ራእይ መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን ለማድረግ በመወሰን ተግባራዊ ልናደርገው እንችላለን፡፡ የእግዚአብሔር ቅድስና በባህርዩ ይህንን ይመስላል፡፡ ስለ እግዚአብሔር ቅድስና በተመስጦ ስናስብ፣ መለስ ብለን የተላለፍንባቸውን፣ አሻፈረኝ ያልንባቸውን፣ እግዚአብሔር የተናገረንን ቸል በማለት እርሱን ክብር በሚያሳጣ መንገድ ሕይወታችንን ግራ ለመጋባትና ለመመሰቃቀል አሳልፈን የሰጠንባቸውን በግል ሕይወታችን የተከናወኑ ተግባራትን ልንቃኝ ይገባል፡፡ በእኔ ላይ ሊያርፍ ይገባው የነበረ ይህ ሁሉ የበቀል በትር በክርስቶስ ትከሻ ላይ ማረፉንና እርሱም በፅናት የተሸከመው መሆኑን መለስ ብለን ልናስብ ይገባል፡፡ ያም ሁኔታ የእኔ በደል ምን ያህል አሰቃቂ እንደነበር፣ ሊሰረይም የሚችለው ሰው በሆነው በእግዚአብሔር ልጅ በእኔ ምትክ መሞት ብቻ እንደሆነ ይነግረኛል፡፡ ከእግዚአብሔር ቅድስና አንፃር የእኔ ኃጢአት ምንኛ አሰቃቂ እንደሆነና ሊያስወግደውም የሚችለው ምን እንደሆነ ስረዳ፣ ኃጢአትን በእጅጉ እጠየፈዋለሁ፣ ፀፀቴም ጥልቅ ይሆናል፣ ከዚያም ውስጥ ለእግዚአብሔር ቅድስና ያለምንም ገደብ ራሴን የመስጠቴ ልባዊ መሻት ደግሞ ደጋግሞ በሕይወቴ ስፍራን መያዝ ይጀምራል፣ ስርየት የግድ አስፈላጊ እንዲሆን የሚያደርጉትንም ኃጢአቶች ምን ያህል እንደተጠየፍኳቸው ለእግዚአብሔር እነግረዋለሁ፡፡ [ዶ/ር ጄ.አይ.ፓከር]*

አማኝም ሆንን አልሆንን፣ ለእያንዳንዱ ሰው ሕይወት የእምነትና የሰባራነት ሁኔታዎች አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ክርስቶስን የሕይወታቸው ጌታ አድርገው ላልተቀበሉ ሰዎች፣ ለኃጢአታቸው ይቅርታን ለመቀበል ወደ እግዚአብሔር ሊመጡና በክርስቶስ የሆነውን አዲስ ሕይወት ሊጀምሩ የሚያስችሏቸው ዕድሎች ናቸው፡፡ የጌታ ለሆንን ለእኛ ደግሞ፣ ዘላቂ በሆነው በእምነት ሕይወት ልንመላለስ እንደሚገባን፣ አሁን በምንሠራቸው ኃጢአቶች በእውነት ማዘናችንን የምንገልጥባቸው፣ በየዕለቱም ይቅርታንና መንፃትን የምንቀበልባቸው ማሳሰቢያዎቻችን ናቸው፡፡

ይቅርታን ለማግኘት የሚያስፈልጉት ቅድመ ሁኔታዎች እግዚአብሔር በልቡናችን ውስጥ እምነትንና የተሰበረ መንፈስን ሊያፈስልን አስፈላጊ መሆኑን ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ ይቅርታን የምንቀበልበትን መንገዱን እንመልከት፡፡

# መንገድ

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች ጸጋ በምንቀበልበት መንገድና በጸጋ መሠረት መካከል ያለውን ልዩነት መረዳት ሲሳናቸው ይገኛሉ፡፡ በውጤቱም፣ ጸጋን የመቀበያ መንገድን ጸጋን የይገባኛል ጥያቄ የሚያነሱበት አድርገው በተሳሳተ መንገድ ወደ መጠቀሙ ወይንም ይባስ ብሎ እግዚአብሔር ጸጋን ሊሰጠኝ ይገባል ብለው ወደ ማስገደዱ ያዘነብላሉ፡፡ እንግዲያው፣ በመንገድና በመሠረት መካከል ያለውን ልዩነት ጥርት አድርጎ መረዳት ይገባል ማለት ነው፡፡ ይህንን ልዩነት ለመመልከት ያስችለን ዘንድ፣ ከደረሰበት አደጋ ለማገገም አካላዊ ሕክምና ስለ ፈለገ ሰው እናስብ፡፡ ህክምናው ውድ በመሆኑ፣ በአንድ ድጋፍ ሰጪ ወገን ወጪው ተሸፈነ፡፡ ምናልባት ሰውየው የዳነበት መንገዱ ህክምናው ነው ብለን ማለት እንችላለን፡፡ ለዚህ መዳን መሠረት የሆነው ግን በእርዳታ የተገኘው ገንዘብ ነው፡፡

መሠረት ማለት አንድ ድርጊት ወይንም ውጤት ያረፈበትን አውድማ ወይንም መገባት የሚያመለክት ሲሆን፣ መንገድ ግን ያ ድርጊት ወይንም ውጤት የተከናወነበትን መሣሪያ ወይንም ዘዴ የሚያሳይ ነው በማለት ልዩነቱን ልናጠቃልለው እንችላለን፡፡

ነገሩን ከእግዚአብሔር ይቅርታንና ጸጋን ወደ መቀበል ስናመጣው፣ መሠረቱ ሁል ጊዜም የሚያርፈው በመታዘዝ ሕይወቱና በመስቀል ላይ ባከናወነው መስዋዕታዊ ሞቱ ባስገኘው በክርስቶስ የተገባው መሆን ላይ ነው፡፡ ይህንንም ማቴዎስ ምዕራፍ 26 ቁጥር 28፤ ቆላስይስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 13 እና 14 እና 1ኛዮሐንስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 12 በመሳሰሉ ክፍሎች ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ ይቅርታ ለዘወትር ተገኝቷል፡፡ የተገኘው ግን በክርስቶስ እንጂ በእኛ አይደለም፡፡ ስለዚህ ጸጋ ሁሉ በእኛ ሕይወት ሊተገበር የሚችልበት መሠረታዊ መንገዱ እምነት ነው፡፡ ለእግዚአብሔር በቀጥታም ይገለጥ፣ አሊያም በጸጋ መንገድ በኩል፣ እግዚአብሔር ጸጋንና ሌሎችንም በረከቶች በሕይወታችን የሚያፈስበት ቀዳሚ መሣሪያ እምነት ነው፡፡

እምነት በቀጥታ የሚሠራባቸውን መንገዶች ቅዱሳት መጻሕፍት ይዘረዝራሉ፡፡ ከዚህ ትምህርታችን ዓላማ አንፃር፣ እነዚህን መንገዶች በሁለት ዋና ጎራዎች ጠቅለል አድርገን እናቀርባቸዋለን፣ መነሻችንንም ጸሎትን እናደርጋለን፡፡

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፣ ጸሎት ከእግዚአብሔር ጸጋንና ይቅርታን ለመቀበል ልመና የሚቀርብበት መደበኛ መንገድ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ለምሳሌ፣ መንፈስ ቅዱስ ይቅርታን በሕይወታችን

ተግባራዊ እንዲሆን የሚያደርግበት የእምነት መግለጫ ስለ ሆነው የኑዛዜና የንስሓ ጸሎት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ የእነዚህን መሳይ ጸሎቶች ውጤታማነት በ1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 8 ከቁጥር 29 እስከ 40፤ መዝሙር 32 ከቁጥር 1 እስከ 11፤ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 8 ቁጥር 22፤ 1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 9 እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች እናገኛለን፡፡

ጌታን ወደማወቅ በመጡ አዲስ ሰዎች ሕይወት ውስጥ፣ በእምነት የሚቀርቡ ኑዛዜና የንስሓ ጸሎቶች ይቅርታ እና ለሕይወታቸውም ድነትን እንዲያገኙ መንፈስ ቅዱስ በመጀመሪያ ደረጃ የሚሠራባቸው መንገዶች ናቸው፡፡ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 11 ቁጥር 18 ላይ ቤተክርስቲያን የሰዎችን መለወጥ "ለሕይወት የሚሆን ንስሓ" በማለት የምትጠቅሰው ለዚህ ነው፡፡ ለሚያምኑትም ሁሉ፣ የኑዛዜና የንስሓ ጸሎቶች በሕይወታችን የእግዚአብሔርን ጸጋ የምንቀበልባቸው ወሳኝ መንገዶች ሆነው ይቀጥላሉ፡፡ ይህንንም በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 9 ላይ እናነባለን፡፡

> በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው። (1ኛ ዮሐ 1፥9)

የወንጌል አስደናቂ ዜና ክርስቶስ ስለ እኛ በሠራው ሥራ ምክንያት እግዚአብሔር ኃጢአታችንን በነፃ ይቅር ያለልን መሆኑን ማወጁ ነው፡፡ ይህንንም ይቅርታ በእምነት እንዲሰጠን በመለመን ብቻ መቀበል እንችላለን፡፡

> *ታውቃላችሁ፣ ኃጢአተኞች ወደ እግዚአብሔር በመምጣትና "ሰማያዊ አባት ሆይ፣ ይቅር በለኝ" በማለታቸው ብቻ እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ይቅር ይላል ብለህ ስታስተምር፣ በርካታ ወገኖች ይህማ የእግዚአብሔርን ጸጋ ማቅለል ነው በማለት ያስባሉ፡፡ የጉዳዩ እውነታ ግን፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ እጅግ ላቅ የሚያደርገው መሆኑ ነው፣ ምክንያቱም ንስሓችን ስላዳነን፣ ወይንም እግዚአብሔር ይቅር ያለን ንስሓችንን መሠረት አድርጎ ስለሆነ ሳይሆን፣ ድንበር በማይበጅለት፣ በዋጋ ሊተመን በማይችለው እጅግ ውድ በሆነው በአንድያ ልጁ ሞት ምክንያት እግዚአብሔር ራሱ ይቅር የመባላችንንና የመታረቃችንን መሠረት ስላዘጋጀልን ነው፡፡ [ዶ/ር ጂ. ሊዮን ዱንካን]*

> *ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር ልጅ፣ የሰላሴ ሁለተኛው አካል ወደ ምድር የመጣበትና ሠላሳ የትሕትናና የአገልጋይ ሎሌነትን ሕይወት የኖረበት አልፎም መከራን የተቀበለበትና በመስቀል ላይ የሞተበት እውነታ የኃጢአትን ዘላለማዊ ዕዳ ለመሸከምና በመስቀልም ላይ የኃጢአታችንን ዕዳ ለመክፈል ነው፡፡ ያም ዘላለማዊ፣ ቁጥር ስፍር የሌለው፣ ማለቂያም የሌለው ስለ ኃጢአታችን የተከፈለ ዋጋ ነው፡፡ ስለዚህ በምንም መንገድ ርካሽ ጸጋ ሊሆን አይችልም፡፡ በየትኛውም ዘመን ከተገለጠው ጸጋ እጅግ ውድ የሆነ ዋጋ ያለው ነው፡፡ እኛ*

*በነፃ እንቀበለዋለን፣ የዚህም ብቸኛ ምክንያቱ ኢየሱስ ስለ እኛ ሁሉን ስለሆነልን ነው፡፡ [ዶ/ር ማርክ ስትራውስ]*

*ወደ እርሱ የሚመጡና "ጌታ ሆይ፣ ይቅር በለኝ" የሚሉ ሁሉ ይቅር ይባላሉ፡፡ ይህም የሚሆነው ለይቅርታ የሚያቀርቡት ልመና የተመሰገነ ስለሆነ አይደለም፣ ንስሓቸውም መልካም ስለሆነ አይደለም፣ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማያዊ አባታችን ጋር እንደገና ልንታረቅና ልንገናኝ የምንችልበትን አስፈላጊ ነገር ሁሉ ለእኛ ስላደረገልን ነው፡፡ [ዶ/ር ጄ. ሊዮን ዱንካን]*

አሁን ደግሞ፣ ጥቂት ቆም በማለት የኑዛዜና የንስሓ ጸሎቶች እንደ መደበኛ የይቅርታ መቀበያ መንገዶች ከመሆን ባሻገር፣ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ያልተለመዱ የይቅርታ መቀበያ መንገዶችም ሆነው የሚያገለግሉ መሆኑን ማንሳት ይገባናል፡፡ ምልጃ፡ ፅሞና፤ ወይንም ልመና ወይንም ስለ ሌላ ሰው መጸለይ ተብሎ ሊገለፅ ይችላል፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት የተዋጣለትን የምልጃ ጸሎት ያከናወኑ በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌነት ያላቸውን ሰዎች መዝግበው አስቀምጠዋል፡፡ ይህንንም በዘኁልቁ ምእራፍ 14 ቁጥር 19 እና 20 ላይ፣ እግዚአብሔር የሙሴን ምልጃ አድምጦ የእስራኤልን ኃጢአት ይቅር ባለበት ስፍራ ውስጥ እንመለከተዋለን፡፡ በ2ኛ ዜና ምዕራፍ 30 ከቁጥር 18 እስከ 20 ደግሞ፣ የሕዝቅያስን የምልጃ ጸሎት ተቀብሎ ለፋሲካ በዓል ራሳቸውን በሚገባ ያላዘጋጁትን ሰዎች ጌታ ይቅር ማለቱን እንመለከታለን፡፡ በኢዮብ ምዕራፍ 1 ቁጥር 5 ላይ ደግሞ፣ ኢዮብ ስለ ልጆቹ ዘወትር መስዋዕትን ያቀርብ እንደነበረ እንረዳለን፡፡ በያዕቆብ ምዕራፍ 5 ቁጥር 14 እና 15 ላይም፣ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች የበደሉ ሰዎች ምህረትን እንዲያገኙ እንደሚያደርጉ ባስተማረበትም ክፍል ውስጥም እንመለከተዋለን፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር በታማኝነት የምልጃ ጸሎት የሚጸልዩ ሰዎችን ሰምቶ ሁል ጊዜ መልስ ላይሰጥ ይችላል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግን ምላሽ ይሰጣል፡፡

ከነዚህ ሰብዓዊ ምልጃዎች ባሻገር፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስም ስለ ሰዎች ይማልዳሉ፡፡ የኢየሱስ ምልጃ እንደ ኢሳያስ ምዕራፍ 53 ቁጥር 12፤ ሮሜ ምእራፍ 8 ቁጥር 34 እና ዕብራውያን ምዕራፍ 7 ቁጥር 25 በመሳሰሉ ስፍራዎች ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ማላጅነት ደግሞ በሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 26 እና 27 ላይ ተገልጧል፡፡

ሁለተኛው ጥቅል ይቅርታን የመቀበያ መንገዶች ደግሞ ልዩ ልዩ የቤተክርስቲያን ሥርዓቶች ወይንም ዘመነኞቹ የፕሮቴስታንት አብያተክርስቲያናት ጥምቀትና የጌታ እራት (ቅዱስ ቁርባን) ብለው የሚጠሩዋቸው ናቸው፡፡

"ሥርዓት" የሚለውን ቃል ስንጠቀም ግን በሮማ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ስለሚከናወነው የጌታ እራትና የጥምቀት ሥርዓት መናገራችን እንዳልሆነ ግልፅ ልናደርግ ይገባናል፡፡ ከታሪክ

እንደምንረዳው ግን “ሥርዓት” የሚለው ቃል የጌታ እራትንና ጥምቀትን ለማመልከት በበርካታ የፕሮቴስታንት ቤተ እምነቶች ውስጥ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ እነዚህ ሥርዓቶች፣ እምነታችንን የምንገልጥባቸውና የእርሱን በረከት የምንቀበልባቸው እንዲሆኑ አድርጎ እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን የሰጣቸው ልዩና የተቀደሱ ሥርዓቶች ናቸው፡፡ ከእነዚህ ሥርዓቶች ዝርዝር አፈፃፀሞች አንፃር በበርካታ ፕሮቴስታንቶች ዘንድ ያሉ ልማዶች ይለያያሉ፡፡ ሁሉም ግን በአንድ መንገድ ልዩ በመሆናቸው ላይ ይስማማሉ፡፡

አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች የጌታ እራትና ጥምቀት ይቅርታን የመቀበያ መንገዶች እንደሆኑ አድርገው አንዳንዶች ሲናገሩ ሲሰሙ ጥርጣሬ ያድርባቸዋል፡፡ ስለዚህ፣ እነዚህ ሥርዓቶች ውጤታማ የሚያደርጋቸው በራሳቸው የሆነ ብቃት አላቸው ብለን እያልን እንዳልሆነ አፅንዖት መስጠት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በምንም መንገድ የይቅርታ መሠረት ሊሆኑ አይችሉም፡፡

በተመሳሳይ፣ በጥምቀትና በጌታ ራት አማካይነት ማመናችንን ስንገልፅ፣ መንፈስ ቅዱስ እነዚህን ስርዓቶች የእግዚአብሔርን ይቅርታ በሕይወታችን ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚጠቀምባቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡

በማርቆስ ምዕራፍ 1 ቁጥር 4፣ በሐሥ ምዕራፍ 2 ቁጥር 38፣ ሮሜ ምእራፍ 6 ከቁጥር 1 እስከ 7 እና በቆላስያስ ምዕራፍ 2 ከቁጥር 12 እስከ 14 በመሳሰሉት ክፍሎች ውስጥ ጥምቀት ፀጋን የመቀበያ መንገድ እንደሆነ ዓይነት ተገልጧል፡፡

ለምሳሌ አንዱን ብናነሳ፣ በሐሥ ምዕራፍ 22 ቁጥር 16 ላይ ሐናንያ ለጳውሎስ የተናገረውን አድምጡ፡

> አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ። (ሐሥ 22፥16)

በዚህ መመሪያ ውስጥ፣ የጳውሎስ ኃጢአት በጥምቀት አማካይነት “እንደሚታጠብ” ወይንም ይቅር እንደሚባል ሐናንያ ያመለክታል፡፡

እንግዲህ፣ በእርግጥ፣ ጥምቀት ይቅርታን የመቀበያ መሠረት አይሆንም፡፡ ይቅርታን የምንቀበልባቸው ሌሎችም መንገዶች አሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ከክርስቶስ ጋር ከተሰቀሉት ሌቦች አንዱ ሲያምን ጨርሶውኑ አልተጠመቀም፡፡ ሆኖም ግን፣ ሉቃስ ምዕራፍ 23 ቁጥር 43 ምህረትን እንደተቀበለና እንደዳነ አመልክቶናል፡፡ ስለዚህ፣ ምህረትና ድነት የሚያገኙት የተጠመቁ ብቻ ናቸው ብለን በተሳሳተ መንገድ እንዳናስብ ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡ አሁንም፣ ቅዱሳት መጻሕፍት በስፋት በግልፅ የሚያስቀምጡት ጥምቀት የተቀበልነውን ምህረት በሕይወታችን በተግባር መገለጥ መጀመሩን የምናሳይበት መሆኑን ነው፡፡

እውነታው በጌታ ራትም ተመሳሳይ ነው፡፡ የጌታን ራት መካፈል የክርስቶስን ሞት ትሩፋት መቀበያ መንገዱ መሆኑን ከዚህም አንዱ ይቅርታ መሆኑን ጳውሎስ በግልፅ አስተምሯል፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 16 ምን እንደፃፈ አድምጡ፡

> የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቆርሰውስ እንጀራ ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን? (1ኛቆሮ 10፥16)

እነዚህ ምላሽ የማይሰጥባቸው ጥያቄዎች ናቸው፡፡ የጳውሎስን ደብዳቤ የሚያነብብ ሁሉ፣ መልሶቹ "አዎን፣ እርግጥ ነው፡፡" የሚሉ እንደሚሆኑ ያውቃል፡፡ የጌታን እራት በእምነት ስንወስድ ከክርስቶስ ጋር እንተባበራለን፡፡

የኃጢአት ይቅርታ በክርስቲያናዊ የሕይወት ዘመናችን ሁሉ የምናጣጥመው የድነት ትልቅ በረከት ነው፡፡ አዲስ የተለወጥንም እንሁን ወይንም እድሜ ዘመናችንን ሁሉ በአማኝነት የዘለቅን፣ ይቅር መባላችን ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር የሚኖረን ጉዞ ዘላቂ ገፅታ ነው፡፡ በፍፃሜውም በሌሎች በርካታ በረከቶችም የሚታጀብ ይሆናል፡፡

ከ1703 እስከ 1791 የኖረውና የሜቶዲስት ቤተክርስቲያን መሥራች የሆነው ጆን ዌስሊ፣ የተራራውን ስብከት በገለጣ ባቀረበበት 26ኛው ስብከቱ ስለ ይቅርታ ተናግሯል፡፡ እስኪ ምን እንዳለ አድምጡ፡

> *የኃጢአትን ይቅርታ ስንቀበል ወዲያውኑ... ከተቀሩት ቅዱሳን ጋር በእምነት በእርሱ ውስጥ ያለውን ሁሉ እንቀበላለን፡፡ ኃጢአት አቅመ ቢስ ይሆናል፡፡ ማለትም፡ በጸጋ ስር ባሉት ላይ፣ ያም ማለት በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ ባገኙት ላይ አይሰለጥንም፡፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉትም ኩነኔ አይኖርም፣ ስለዚህም ከኃጢአትና ከኩነኔ ነፃ ናቸው፡፡ የህጉ ጽድቅ በውስጣቸው ተፈፅሟል፣ ስለዚህ እንደ ሥጋ ፈቃድ ሳይሆን እንደ መንፈስ ፈቃድ ይመላለሳሉ፡፡ [ጆን ዌስሊ]*
>
> *እኔ እንደማስበው፣ የኃጢአት ይቅርታ ማለት፣ በአንዳንድ መንገዶች፣ እንደክርስቲያኖች ካገኘናቸው የከበሩ እውነታዎች የላቀው ነው፡፡ በመሠረታዊነትም ኃጢአታችንን ይቅር ተባልን ማለት ከፈጣሪያችን ከእግዚአብሔር ጋር የሰመረ ግንኙነት ኖረን ማለት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት የምንኖርባትን ዓለም ስንቃኝ፣ ሰዎች የመኖርን ትርጉም፣ ቁም ነገርን እና ዓላማን ለማግኘት ሲዋትቱ እናገኛቸዋለን፡፡ በየባህሎቻችንም በርካታ ግራ መጋባቶች አሉ፡፡ ለመሆኑ ሕይወት ምንድን ነው? የመኖር ምክንያቱስ ምንድን ነው? ለምን እዚህ ተገኘሁ? ስለዚህ ሰዎች ቁም ነገርንና የመኖርን ትርጉም ለማግኘት አለ ያሉትን ነገር ሁሉ ማለትም*

*ሥራ፣ የፍትወተ ሥጋ እርካታ ወይንም ዕፅ ይሞክራሉ፡፡ ማለቴም ሰዎች ደስታና ሃሴት ይገኙባቸዋል ብለው የሚያስቡዋቸው በርካታ መንገዶችና ስፍራዎች ሞልተዋል፡፡ ወንጌል ግን እንደ ሰብዓዊ ፍጡራን የሚያስፈልገን አንድ መሠረታዊ ነገር ከሠሪያችን ከአንዱ ጋር፣ ከፈጣሪያችን ጋር በሰመረ ግንኙነት ውስጥ መገኘት ነው በማለት ይነግረናል፡፡ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን፣ ኢየሱስ ክርስቶስን፣ ኃጢአታችን ያስተሰርይና የእግዚአብሔርንም ቁጣ በላዩ ይሸከም ዘንድ ላከው በማለት ወንጌል ይነግረናል፡፡ እግዚአብሔር ከፍቅሩ የተነሳ ኃጢአታችንን ያስተሰርይ ዘንድ ልጁን ላከ፣ ስለዚህ እምነታችንን በእርሱ ላይ ስናደርግ የኃጢአታችንን ይቅርታ እንቀበላለን፡፡ ወደዚህ ልምምድ ስንመጣ፣ ይህንን መሳይ ይቅርታ ለመቀበል ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘወር ስንል፣ አስደናቂ ሰላም በውስጣችን ይፈስሳል፣ ከዓለምም ጋር ስምም እንሆናለን ምክንያቱም ለዓለም እውነተኛው ትክክለኛነት የሚመነጨው ከዚያ ብቻ ነውና፡፡ ይህም ሲሆን በእውነት የተፈጠርነው ይህንን ለመሰለው ሰላም እንደነበር እንረዳለን፡፡ የተፈጠርነው ከእግዚአብሔር ጋር በሰመረ ግንኙነት ለመኖር ነው፡፡ ይህንን የምንረዳው ግን በዚያች ቅፅበት ይሆናል፡፡ [ዶ/ር ቶም ሼሬነር]*

የኃጢአትን ይቅርታ አስተምህሮ ተመልክተናል አሁን ደግሞ ቀጣዩን የእምነት አንቀጻችን ክፍል የሆነውን የሥጋ ትንሣኤ ለመመልከት እንዘጋጃለን፡፡

# 3. ትንሣኤ

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ የሰፈረውን መልሰን እንቃኘው፡

*በሥጋ ትንሣኤ*

*አምናለሁ፡፡*

በዚህ ነጥብ ላይ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው የሚናገረው ስለ ኢየሱስ ትንሣኤ እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባል፡፡ የኢየሱስ ትንሣኤ በሃይማኖት መግለጫው መጀመሪያ ላይ በሦስተኛው ቀን ከሙታን በተነሣ በሚል ተቀምጧል፡፡ የሃይማኖት መግለጫው ስለ "ሥጋ ትንሣኤ" ሲናገር ስለ አጠቃላይ ትንሣኤ ማለትም ክርስቶስ በክብር ሲመለስ ሰው ሁሉ የሚነሣ መሆኑን ለማመልከት ነው፡፡

## እርግማን

አጠቃላዩን ትንሣኤ በሦስት ደረጃዎች እንመለከተዋለን፡፡ በመጀመሪያ አካላችንን ለሞት የዳረገውን እርግማን እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ የክርስቲያኖች ወንጌል ለአካላችን ሕይወት ተገኘ

ያለበትን ሃሳብ እናብራራለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በስተመጨረሻ ሰውነታችን የተቤዠበትን መንገድ እንመለከታለን፡፡ እስኪ አካላችንን ለሞት የዳረገውን እርግማን አስቀድመን እንመልከት፡፡

ቀደም ባለው ትምህርታችን፣ እግዚአብሔር የሰውን ዘር የሚታይ አካል እና የማትታይ ነፍስ አድርጎ እንደፈጠረው ተመልክተናል፡፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 4 ቁጥር 12 እና 1ኛ ተሰሎንቄ ምዕራፍ 5 ቁጥር 23 በመመሥረት፣ አንዳንድ ትውፊቶች እያንዳንዱ የሰው ዘር ከነፍስ በተጨማሪ መንፈስም አለው ብለው አቋም ይይዛሉ፡፡ ነገር ግን ወደ 200 የሚጠጉ ጥቅሶች እነዚህ ቃላት በተለዋዋጭነት የውስጥ የማይታይ ጠቅላላ ማንነታችንን ለመግለጥ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ፣ ብዛኞቹ ክርስቲያናዊ ትውፊቶች "ነፍስ" እና "መንፈስ" የሰውን ውስጣዊ ማንነት የሚገልጡ በመሆናቸው ላይ ድምዳሜ አድርገዋል፣ እናም የሰው ዘር ሁለት ዋና ክፍሎች ብቻ አሉት፡ አካልና ነፍስ፡፡

በኃጢአት ከመውደቃችን አስቀድሞ፣ አካላችንና ነፍሳችን በኃጢአት በማርከስ ኃይሉ ያልተበከሉ ነበሩ፡፡ አዳምና ሔዋን ኃጢአትን ሲሠሩ ግን፣ ኃጢአት ነፍሳቸውን ብቻ ሳይሆን፣ አካላቸውንም አረከሰ፡፡ ይህም አካላዊ መርከስ በፍፃሜውም ለአካላዊ ሞት ዳረጋቸው፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 19 ላይ እግዚአብሔር አዳምን የረገመውን እርግማን አድምጡ፡

> ወደ ወጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ አፈር ነህና፥ ወደ አፈርም ትመለሳለህና። (ዘፍ 3፥19)

አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ሲበድሉ፣ ሁለቱንም ረገማቸው፡፡ የእርግማኑም አንድ ክፍል ሟች መሆናቸው ነው፡፡ በመጨረሻ ይሞቱና ወደ አፈር ይመለሳሉ፡፡ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 12 እንደጻፈው የሰው ዘር በጠቅላላ የአዳምና የሔዋን ዝርያ በመሆኑ ምክንያትም፣ ሁላችን በተመሳሳይ አመፃ ተወለድን፡፡

> ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤ (ሮሜ 5፥12)

ኃጢአት በአዳምና በሔዋን ላይ ተፅዕኖ ያሳደረው በአካላዊም በመንፈሳዊም መንገድ ነው፡፡ እኛም የእነርሱ ዝርያዎች በመሆናችን ምክንያት፣ ያው እርግማን ደርሶብናል፡፡ ነፍሳችን ወደ ዓለም የመጣችው መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ሞት ብሎ በሚያስቀምጠው ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡ ሁላችንም በእግዚአብሔር ፍርድ ስር ወድቀናል፣ እርሱንም ደስ የምናሰኝበት አቅም የለንም፡፡ ስለዚህም ሁኔታ ሮሜ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 12 እስከ 19 እና ምዕራፍ 8 ከቁጥር 1 እስከ 8 በመሳሰሉ ምንባቦች ውስጥ እናነባለን፡፡

ልክ እንደ አዳምና እንደ ሔዋን ሁሉ፣ የእኛም አካል በኃጢአት የረከሰ ነው፡፡ ይህም መርከስ አካላዊ ስቃይ፣ ህመም እና በፍፃሜውም ሞት አስከተለብን፡፡ ጳውሎስ ስለዚህ ጉዳይ በሮሜ ምዕራፍ 6 ከቁጥር 12 እስከ 19 እና ምዕራፍ 7 ከቁጥር 4 እስከ 25 ላይ ተናግሯል፡፡ ኃጢአት ማንታችንን እንዳለ አርከሶታል ማለትም አካላችንንም ነፍሳችንንም ማለት ነው፡፡ የእግዚአብሔር አስደናቂ ተስፋ ግን በክርስቶስ ያገኘነው ድነት አካላችንንም ነፍሳችንንም የተቤዠ መሆኑ ነው፡፡

*ክርስቲያኖች ሰብዓዊ ሞትን እንደ መደበኛ ሁኔታ ሊቆጥሩ ጨርሶ አይገባም፡፡ ብዙ ጊዜ በተለምዶ አነጋገራችን ይህንን መሳይ ቋንቋ እንጠቀማለን ወይንም ተመሳሳይ ሃሳብ እናንፀባርቃለን፡፡ አንዳንድ ጊዜ በቀብር ላይ ስለ አንድ ሰው "መልካም ረጅም ዕድሜ ጠግቧል መቼም ሞት አይቀር" እንላለን፡፡ ምናልባት ለጋ ህፃን ልጅ ሲሞት፣ በሃያዎቹ ወይንም በሠላሳዎቹ ዓመታት ውስጥ ያለ ወጣት ሲሞት ግን "አ፣ እጅግ አሰቃቂ ነው" እንል ይሆናል፡፡ ይህ ግን በፍፁም ሊሆን የሚገባው ክርስቲናዊ አመለካከት አይደለም፡፡ ክርስቲያን ስለ ሞት ያለው አመለካከት ምንም ሆነ ማን ሞት አግባብነት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ገና ከጅማሬው የተፈጠርነው ዘላለም ለመኖር ነበር፡፡ እስኪ አስቡ፣ እግዚአብሔር ገና በፍጥረት ጅማሬ፣ በሰባተኛው ቀን አርፏል፡፡ ይህም የሚያመለክተን ከመላው ፍጥረቱ ጋር ምሉዕ ወደ ሆነ ደስታ የገባ መሆኑን ነው፡፡ እኛም በክብሩ ውስጥ እንኖር በፍጥረትም ላይ የተሰጠንን ሥልጣን እንገለገልበት ነበር፡፡ እኛ ጨርሶውኑ ለሞት አልተፈጠርንም፡፡ ሆኖም ግን ጳውሎስ እንደሚናገረው፣ በዘፍጥረት ሁለት ማስጠንቀቂያ የተሰጠበት ሞት በዘፍጥረት 3 እንደተገለጸው ወደ ዓለም በገባው ኃጢአት ምክንያት መጣ፣ የኃጢአትም ደመወዝ ሆነ፡፡ ይህም ሞት አካላዊም መንፈሳዊም ሞት ነው፡፡ [ዶ/ር ስቴፋን ዌሉም]*

በአንድ መንገድ፣ አካላዊ ሞት ለእኛ ለምናምነው በረከት ነው ምክንያቱም ወደ ክርስቶስ እንወሰዳለንና፡፡ከዚህ ላቅ ባለው መሠረታዊ እውነታ ግን አካላዊ ሞት እጅግ አሰቃቂ ነው፡፡ አዎን ዓለም አቀፋዊ አይቀሬ ነገር ነው፣ ሆኖም ደግሞ አሰቃቂና ኢ-ተፈጥሯዊም ነው፡፡ እግዚአብሔር የሰውን ዘር ለሞት አልፈጠረውም፤ የፈጠረን ለሕይወት ነው፡፡ እናም ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ አካላዊ መቤዠትን እስክናገኝ ድረስ ድነታችን ምሉዕ አይሆንም፡፡

አካላዊ ሞት ያስከተለብንን እርግማን ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ትንሣኤያችንን ስላረጋገጠልን ወንጌል እንነጋገራለን፡፡

# ወንጌል

በመንግሥተ ሰማያት አካል የሌላቸው መናፍስቶች ሆነን እንኖራለን የሚል መረዳት ያላቸው ክርስቲያኖች ይኖራሉ ብለን የምናምን ምን ያህል እንሆን? ምንልባት ከጥቂትም እጅግ ያነሰን ልንሆን እንችላለን፡፡ ምናልባት ነገሩ ግራ ቢመስልም፣ በዘመነኞቹ ቤተክርስቲያናት ውስጥ

የትምህርተ ትንሣኤ ሙታን በአብዛኛዎቹ የማይታወቅ ይመስላል፡፡ ለዚህም ምክንያት ከሆኑት መካከል አንዱ ክርስቲያኖች የሰብዓዊ አካላችንን ወሳኝነት በአግባቡ መረዳት አለመቻላቸው ነው፡፡ የምሥራቹ ግን ቅዱሳት መጻሕፍተ በግልፅ እንደሚያስተምሩት ክርስቶስ ሲመለስ ንፍሳችን ብቻ ሳትሆን፣ አካላችንም ይከብራል፡፡

# ብሉይ ኪዳን

ሦስት መሠረታዊ ጉዳዮችን በማንሳት አካላዊ ትንሣኤ የወንጌል አካል የመሆኑን ሃሳብ እንዳስሳለን፡፡ በመጀመሪያ፣ የአስተምህሮውን ብሉይ ኪዳናዊ ዳራ እናነሳለን፡፡ ሁለተኛ፣ በአዲስ ኪዳን በግልፅ መታወጁን እንመለከታለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በአማኞች ትንሣኤና በኢየሱስ ትንሣኤ መካከል ስላለው ግንኙነት እንነጋገራለን፡፡ ከብሉይ ኪዳን እንጀምር፡፡

በርካታ የዘመናችን ክርስቲያኖች ይህንን ባይገነዘቡትም፣ ወንጌል የሚለው ቃል፣ ማለትም የምሥራች የሚለው ቃል የመጣው ከብሉይ ኪዳን ነው፡፡ በተለይም፣ በኢሳያስ ምዕራፍ 52 ቁጥር 7 እና በምዕራፍ 61 ቁጥር 1 እና በናሆም ምዕራፍ 1 ቁጥር 15 ላይ እናገኘዋለን፡፡

አንዱን ለምሳሌ ለማንሳት ኢሳያስ ምዕራፍ 52 ቁጥር 7 እናዳምጥ፡

> የምስራች የሚናገር፥ ሰላምንም የሚያወራ፥ የመልካምንም ወሬ የምስራች የሚናገር፥ መድኃኒትንም የሚያወራ፥ ጽዮንንም። አምላክሽ ነግሦአል የሚል ሰው እግሩ በተራሮች ላይ እጅግ ያማረ ነው። (ኢሳ 52፥7)

በብሉይ ኪዳን፣ “የምሥራች” ወይንም “ወንጌል” ማለት እግዚአብሔር የእርሱን እና የሕዝቡን ጠላቶች በማሸነፍ የእርሱን ሕዝብ ያድናል ማለት ነው፡፡ ጠበብ ባለው አመለካከት፣ የምሥራች ማለት የምድር ጠላቶቻቸው ከሚያሳድሩባቸው ጭቆና ሕዝቡን እግዚአብሔር ነፃ ያወጣል ማለት ነው፡፡ ሰፋ ባለው ሁኔታ ግን፣ በአዳምና በሔዋን ውድቀት ምክንያት የመጣውን እርግማን እግዚአብሔር የሚያስወግድ መሆኑ እርሱ የምሥራች ነው፡፡ በሰማያት ያለውን የከበረ ንግሥናውን በምድር ሁሉ ላይ ያስፋፋል በመጨረሻም በእርሱ ያመኑትን ይባርካል፡፡

እርግጥ ነው፣ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የሰጠው ድነት የሚመሠረተው በክርስቶስ የወደፊት ድል ላይ ነው፡፡ ምንም እንኳን ክርስቶስ ለኃጢአት ለመሞት ገና ያልመጣ ቢሆንም፣ ስለ ህዝቡ እንደሚሞት ግን ተስፋ ሰጥቶ ነበር፡፡ ያም ተስፋ ድነታቸውን ለማረጋገጥ በቂ ነበር፡፡ በብሉይ ኪዳን የተነገረ እያንዳንዱ የድነት ተስፋ ወደ ክርስቶስና መጥቶ ወደሚፈጽመው ሥራ ያመለክታል፡፡

ዕብራውያን ምዕራፍ 10 ከቁጥር 1 እስከ 5 የብሉይ ኪዳንን መስዋዕት የገለጠበትን መንገድ አድምጡ፡

> ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፥ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈጽም ከቶ አይችልም።
> እንደዚህማ ባይሆን፥ የሚያመልኩት አንድ ጊዜ ነጽተው ከዚያ በኋላ በሕሊናቸው ኃጢአትን ስላላወቁ ማቅረብን በተዉ አልነበረምን?
> ነገር ግን በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት መታሰቢያ አለ፤
> የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን እንዲያስወግድ የማይቻል ነውና።
> ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ። መሥዋዕትንና መባን አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ፤ (ዕብ 10፥1-5)

የዕብራውያን ፀሐፊ የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች ኋላ በክርስቶስ የሚገለጠው እውነታ ጥላ ብቻ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ የእንስሳቶቹ መስዋዕት በፍፁም ኃጢአትን ሊያስተሰርይ አይችልም ምክንያቱም የሰው ኃጢአት ሊቀጣ የሚገባው በሰው ሞት እንደሆነ እግዚአብሔር ደንግጓል፡፡ ነገር ግን ሞቱ ሙሉ በሙሉ ሰብዓዊ ሞት ስለሆነ፣ ኃጢአትን ለማስተሰረይ ፍፁም ብቃት ወዳለው ወደ ክርስቶስ ያመለክታሉ፡፡

በብሉይ ኪዳን እንደሚገኝ የወንጌል አካል፣ በሞት የተለዩ ሰብዓዊ ፍጡራንን ሁሉ እግዚአብሔር ከሞት እንደሚያስነሳቸውና እንደሥራቸውም እንደሚፈርድባቸው የእግዚአብሔር ህዝብ ተምሯል፡፡ በጽድቅ የኖሩ፣ በእግዚአብሔርም ያመኑ ለዘላለም ይባረካሉ፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ያመፁት ግን ይፈረድባቸዋል ለዘላለምም ይቀጣሉ፡፡ እነዚህ ሁለቱም ፍፃሜዎች በአካላዊ ቅርፅ ለዘላለም ይከናወናሉ፡፡ ክርስቲያን የነገረ መለኮት ምሁራን ይህን ክስተት ከመጨረሻው ፍርድ ጋር ያገናዝቡታል፡፡

ቀደም ባለ ትምህርት እንደተመለከትነው፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ስለ መጨረሻው ፍርድ እንዲህ ጠቅሷል፡

> *ከዚያም በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በሚመለስ*

የመጨረሻው ፍርድ አካላዊ ትንሣኤን የሚያካትት መሆኑ የተገለጠበት ሃሳብ በዳንኤል ምዕራፍ 12 ላይ ይገኛል፡፡ በዚያም ስፍራ በሚመጣው ዘመን እግዚአብሔር ህዝቡን ከግዞት እንደሚያወጣ መልአኩ ለዳንኤል ገልጦለታል፡፡

በዳንኤል ምዕራፍ 12 ቁር 1 እና 2 ለዳንኤል የተነገረውን አድምጡ፡

በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል
ይነሣል ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ
ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው
ሕዝብህ ሁሉ እያንዳንዱ ይድናል።
በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ እኵሌቶቹ ወደ
ዘላለም ሕይወት፥ እኵሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቍልና።
(ዳን 12፥1-2)

በምድር ትቢያ ውስጥ ስላንቀላፉት በተነገረው ውስጥ ስለ አካላዊ ትንሣኤ ለዳንኤል በግልጽ ተነግሮታል፡፡ ነፍስ በምድር ትቢያ ውስጥ አታንቀላፋም፤ አካል ግን ያንቀላፋል፡፡ በመጨረሻው ፍርድ የሚነሱት እነዚያ አካላት ናቸው፡፡

ኢሳያስም በመጨረሻው የፍርድ ቀን አጠቃላይ ትንሣኤ እንደሚሆን ተናግሯል፡፡ በኢሳያስ ምዕራፍ 26 ከቁር 19 እስከ 21 የጻፈውን እስኪ አድምጡ፡

ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ፥ ሬሳዎችም ይነሣሉ። በምድር የምትኖሩ ሆይ፥
ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና፥ ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ
ዘምሩም።
ሕዝቤ ሆይ፥ ና ወደ ቤትህም ግባ፥ ደጅህን በኋላህ ዝጋ ቍጣ እስኪያልፍ
ድረስ ጥቂት ጊዜ ተሸሸግ።
በምድር በሚኖሩት ላይ በበደላቸው ምክንያት ቍጣውን ያመጣባቸው
ዘንድ፥ እነሆ፥ እግዚአብሔር ከስፍራው ይወጣል ምድርም ደምዋን
ትገልጣለች፥ ሙታኖችዋንም ከእንግዲህ ወዲህ አትከድንም።
(ኢሳ 26፥19-21)

በምድር ትቢያ ውስጥ ያንቀላፉ ሁሉ፣ ልክ ምድር አዲስ ልደት እንደቸረቻቸው ዓይነት ከመቃብሮቻቸው ውስጥ በአዲስ ሕይወት እንደሚነሱ እንደገና ተመልክተናል፡፡ ይህም የሚከናወነው በፍርድ አውድ ውስጥ ማለትም ጌታ በምድር በሚኖሩ ሰዎች ላይ በኃጢአታቸው ሊፈርድ ሲመለስ ነው፡፡

ትምህርተ ትንሣኤ በተጨማሪም በተለያዩ የብሉይ ኪዳን ምንባቦች ውስጥ በፍፃሜ ፍርድ ከሲዖል በማምለጥና በመካስ አውድም እንድምታ እንዳለው ተጠቅሷል፡፡ ይህንንም መዝሙር 49 ከቁጥር 7 እስከ 15 እና መዝሙር 73 ከቁጥር 24 እስከ 28 በመሳሰሉት ውስጥ እናገኘዋለን፡፡ በኢዮብ ምዕራፍ 19 ከቁጥር 25 እስከ 27 ላይም ኢዮብ በፍርድ ቀን ጌታ በምድር ላይ መጥቶ ሲቆም እግዚአብሔርን ለማየት እንደሚነሳ በልበ ሙሉነት እምነቱን ሲገልፅ እንመለከታለን፡፡

*ወደፊት የሚሆነው ትንሣኤና ፍርድ በአዲስ ኪዳን እንደምናየው በብሉይ ኪዳን ግልፅ አይደለም፡፡ ሆኖም ይህ ነገር እንደሚሆን የሚያመለክቱ ፍንጮች በብሉይ ኪዳን ውስጥም ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ኢሳያስ ሙታን እንደሚነሱ፣ ከየመቃብሮቻቸውም እንደሚወጡ ይናገራል፡፡ ዳንኤልም ስለተመሳሳዩ ጊዜ ሲናገር፣ ሙታን ይነሣሉ፣ ጻድቃንና ኃጥአንም በፍፃሜው ፍርድ ፊት ይቀርባሉ ብሏል፡፡ ምንም እንኳን በሁሉም ውስጥ ባይሆንም፣ በጥቂት አይሁዳውያን ውስጥ እያቆጠቆጠ የመጣ ጉዳይ ነበር፡፡ በኢየሱስ ዘመን የነበሩ ፈሪሳውያን በትንሣኤ ያምኑ ነበር፡፡ ሰዱቃውያን ግን ኢያምኑም ነበር፡፡ ሰዱቃውያን ወደ እርሱ መጥተው ነገሩ የማይታመን መሆኑን ለማሳየት አሳቻ ጥያቄ ጠይቀውት በነበረ ወቅት፣ ኢየሱስም ከአንድ ምንባብ በመጥቀስ "እኔ የአብርሃም፣ የይስሃቅና የያዕቆብ አምላክ ነኝ" በማለት እግዚአብሔር ሲናገር "እግዚአብሔር የሕያዋን እንጂ፣ የሙታን አምላክ አይደለም" ብሏቸው ነበር፡፡ እንግዲያው፣ እግዚአብሔር ከአንድ ሰው ጋር ግንኙነት ሲመሠርት፣ ግንኙነቱም ከአንድ ሰው ጋር የቃል ኪዳን ግንኙነት ሲሆን፣ ግንኙነቱ በእውነት ከዚያ ሰው ጋር የሚደረግ የግል ግንኙነት ነው እናም አብርሃም እንዲያው በትቢያ ውስጥ አርፎ የሚቀር ከሆነና ዳግም የማይነሣ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር በዘላላም ቃል ኪዳን ግንኙነት ውስጥ ነው ማለት ትርጉም የለሽ አይሆንምን? ስለዚህ፣ ያ ማለት አዲስ ኪዳን በጠቅላላው በማይሻር ሁኔታ የሚያወሳው፣ ስለ ትምህርተ ዳግም ትንሣኤ ነው ማለት ነው፡፡ በመሠረቱም የኢየሱስ ትንሣኤ የጉዳዩ የፍፃሜ ማኅተም ሆኗል፡፡ [ዶ/ር ጆን ኤም. ፍሬም]*

አጠቃላዩ ትንሣኤ በብሉይ ኪዳን የተገለጠው ወንጌል ክፍል ስለመሆኑ ካወሳን ዘንድ፣ አሁን ደግሞ የአዲስ ኪዳኑም የወንጌል መልዕክት አካል ስለመሆኑም እናውሳ፡፡

# አዲስ ኪዳን

በብሉይ ኪዳኑና በአዲስ ኪዳኑ የወንጌል አዋጆች መካከል ያለው ትልቅ ልዩነት በአዲስ ኪዳን፣ መሲሁ ራሱ በፍፃሜው የመጣ መሆኑ ነው፡፡ በታሪክ ውስጥ የናዝሬቱ ኢየሱስ ተብሎ ተገለጠ፡፡ እግዚአብሔር አሁን በልጁ በኢየሱስ በኩል ነግሡ፡፡ አዲስ ኪዳን ደግሞ ደጋግሞ ኢየሱስ ጌታ ነው የሚለው በዚህ ምክንያት ነው፣ ማለትም እርሱ የነገሡ ንጉሥ ነው ማለቱ ነው፡፡ ይህንንም

እንደ ሉቃስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 11፣ የሐሥ ምዕራፍ 2 ቁጥር 36፣ ሮሜ ምዕራፍ 10 ቁጥር 9 እና 1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 12 ቁጥር 3 በመሳሰሉት ምንባቦች ውስጥ እናገኘዋለን፡፡

*በብሉይም ሆነ በአዲስ ድነት የሚገኘው፣ በእግዚአብሔር መግቦታዊ ቃል ኪዳን በማመን ነው፡፡ ልዩነቱ እምነት በብሉይ ኪዳንና እምነት በአዲስ ኪዳን በእግዚአብሔር ማመን ባለመሆኑ አይደለም፣ ግን ተስፋው ለማን ተሰጠ በሚለው ላይ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን የነበረው እምነት ገና ወደ ፊት ሊፈፀም የተገባውን ተስፋ በእምነት አተኮሮ መመልከት ነበር፡፡ እምነት በአዲስ ኪዳን ግን ተስፋው ወደተፈፀመበት ወደ መስቀሉ መለስ ብሎ መመልከት ነው፡፡ እንግዲያው ሁለቱም፣ እኛ በራሳችን ልናመጣው ወደማንችለውና እርሱ ብቻውን ወደ ሚያከናውነው ወደ እግዚአብሔር መግቦት የሚመራ እምነትን የሚያካትቱ ናቸው፡፡ [ዶ/ር ሮበርት ጂ. ሊስተር]*

ሁሉም የብሉይ ኪዳን የድነት ተስፋዎች፣ በኢየሱስ ተፈፅመዋል፡፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 10 ከቁር 1 እስከ 5 እንደምንመለከተው፣ ሞቱ የብሉይ ኪዳን መስዋዕት ያመለክት የነበረው እውነታ እንደ ነበር እንመለከታለን፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 15 ከቁጥር 8 እስከ 13 እና ገላትያ ምዕራፍ 3 ቁጥር 16 ላይ ደግሞ የኢየሱስ ወንጌል ለብሉይ ኪዳን አባቶች የተገባው ተስፋ ፍፃሜ መሆኑን ጳውሎስ አስተምሯል፡፡ በእነዚህና በሌሎችም በርካታ መንገዶች፣ አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳኑን ወንጌል የሚያፀና ነው፡፡ ያም መለኮታዊ ንጉሥ በፀጋ የሆነውን ድነት በእምነት ለህዝቡ ለመስጠት የሚመጣ የመሆኑ የምሥራች ነው፡፡

አጠቃላዩ ትንሣኤ በመጨረሻው ፍርድ ወቅት እንደሚከናወን ኢየሱስ አስተምሯል፡፡ ለአብነት ያህል፣ በማቴዎስ ምዕራፍ 22 ከቁጥር 23 እስከ 32 እና በሉቃስ ምዕራፍ 20 ከቁጥር 27 እስከ 38 ውስጥ ሰዱቃውያን ትንሣኤ ሙታን የለም ማለታቸውን አስተባብሏል፡፡ በሉቃስ ምዕራፍ 14 ቁጥር 13 እና 14 ላይ ደግሞ በትንሣኤ ቀን እንደ ሥራቸው እንደሚከፈላቸው በማሳየት አማኞች መልካም ሥራን እንዲሠሩ አበረታትቷል፡፡ በዮሐንስ ምእራፍ 11 ከቁጥር 24 እስከ 26፣ ከአልዓዛር እህት ከማርታ ጋር ባደረገው ንግግር አስተምህሮውን አፅንቷል፡፡ በሉቃስ ምእራፍ 20 ቁጥር 37 ኢየሱስ ምን እንዳለ አድምጡ፡

> ሙታን እንዲነሡ ግን ሙሴ ደግሞ በቍጥቋጦው ዘንድ ጌታን የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ በማለቱ አስታወቀ፤ (ሉቃስ 20፥37)

በዚህ ስፍራ፣ የአጠቃላዩ ትንሣኤ አስተምህሮ አስቀድሞውኑ በብሉይ ኪዳንም የተገለጠ መሆኑን ኢየሱስ አመልክቷል፡፡ ይኸው ተመሳሳይ ሃሳብ በአዲስ ኪዳንም ከዳር እስከዳር ተረጋግጧል፡፡ በአሳዛኝ ሁኔታ ግን፣ በአብዛኛዎቹ የአብያተክርስቲያናት ቅርንጫፎች ውስጥ፣ የትንሣኤ ሙታን

ጉዳይ በእጅጉ ቸል ተብሏል፡፡ በርካታ ክርስቲያኖች አካል አልባ መናፍስት ሆነን ለዘላለም እንኖራለን የሚል እምነት አላቸው፡፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 6 ቁጥር 1 እና 2 ላይ ግን፣ ትንሣኤ ሙታን ከክርስትና እምነት መሠረታዊ አስተምህሮዎች አንዱ መሆኑ ተገልጧል፡፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ቁጥር 35 ላይ ደግሞ፣ የአማኞች ትንሣኤ ለመልካም ሥራ የሚያነሳሳቸው ማበረታቻ ሆኖ ተገልጧል፡፡ እንዲያውም፣ ክርስቲያኖች በብሉይ ኪዳን በተሰጠው የሙታን ትንሣኤ ተስፋ እንደሚያምኑ ሐዋርያት ዘወትር ያመለክቱ ነበር፡፡ ለአብነት ያህል፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 4 ቁጥር 1 እና 2 ላይ ይህንኑ አድርገዋል፡፡ ጳውሎስ ደግሞ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 23 ከቁጥር 6 እስከ 8 እና በምዕራፍ 24 ከቁጥር 14 እስከ 21 ላይ ይህንኑ አድርጓል፡፡ አንዱን ለምሳሌ ብናነሳ፣ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 24 ቁጥር 14 እና 15 ላይ ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ እንዴት እንደተሟገተ አድምጡ፡

> ነገር ግን ይህን እመሰክርልሃለሁ፤ በሕጉ ያለውን በነቢያትም የተጻፉትን ሁሉ አምኜ የአባቶቼን አምላክ እነርሱ ኑፋቄ ብለው እንደሚጠሩት መንገድ አመልካለሁ፤
> እነዚህም ራሳቸው ደግሞ የሚጠብቁት፥ ጻድቃንም ዓመፀኞችም ከሙታን ይነሡ ዘንድ እንዳላቸው ተስፋ በእግዚአብሔር ዘንድ አለኝ። (ሐሥ 24፥14-15)

በዚህ ስፍራ፣ ጳውሎስ በመጨረሻው ፍርድ ቀን በአጠቃላይ ትንሣኤ ረገድ ክርስቲያኖች ያላቸው ተስፋ ከአይሁዳውያኑ ተስፋ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን አመልክቷል፡፡ ልዩነቱ ክርስቲያኖቹ ይህ ትንሣኤ የሚፈፀመው በክርስቶስ በኩል ነው ብለው ማመናቸው ነው፡፡

የእግዚአብሔር የድነት ዕቅድ ዘወትር የማይለወጥ መሆኑን መረዳት ለእኛ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለቀድሞይቱ እስራኤል አንድ የመዳን መንገድ፣ ለእኛ ደግሞ ሌላ መንገድ አያዘጋጅም፡፡ ለአይሁድ አንድ የመዳን መንገድ፣ ለአህዛብ ደግሞ ሌላ አያደርግም፡፡ ብሉይና አዲስ ኪዳናት በአስተምህሯቸው አንድ ናቸው፡፡ ክርስቲያኖች ብሉይ ኪዳንን አንዱ የሕይወታቸው ቅርስ አድርገው እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚቀበሉበት አንዱ ምክንያትም ይኸው ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሰዎች የሚድኑት ጥንትም ሆነ አሁን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን በፀጋ ብቻ ነው፡፡ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ለሚታመኑት ህዝቦቹ ዘወትር ያዘጋጀው የምህረትና የመቤዠት ረጅም ታሪክ አንድ ክፍል ናቸው፡፡ መላው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ሁለቱም ኪዳናት፣ ስለዚህ አስደናቂ እውነት ያስተምራሉ፡፡

በአዲስ ኪዳንም ሆነ በብሉይ ኪዳን፣ ወንጌል የሙታን ትንሣኤ የመኖሩን የምሥራች እንደሚያካትት ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ በአማኞች ትንሣኤና በኢየሱስ ትንሣኤ መካከል ስላለው ግንኙነት እንመልከት፡፡

## የኢየሱስ ትንሣኤ

አዲስ ኪዳን በኢየሱስ ትንሣኤና በአማኞች ትንሣኤ መካከል ቢያንስ ሁለት እጅግ ጠቃሚ ግንኙነቶች እንዳሉ ያስተምራል፡፡ በመጀመሪያ፣ ለበረከት ሕይወት እንነሳለን ለዚህም የተለየ ምክንያቱ ከኢየሱስ ትንሣኤ ጋር በመተባበራችን ነው፡፡ ይህም ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 6 ቁጥር 4 እና 5 ላይ እንደ ጻፈው ነው፡፡

> እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም
> በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ
> በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።
> ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል
> ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤ (ሮሜ 6፥4-5)

ጥምቀት በእምነት አማካይነት ከኢየሱስ ሞት ጋር አንድ ሲያደርገን፣ በኃጢአታችን ምክንያት በላያችን ተጭኖ የነበረው ዕዳ እንደተከፈለልን ጳውሎስ አስተምሯል፡፡ ከዚህም ባሻገር ከትንሣኤውም ጋር አንድ ያደረገን ሲሆን በውጤቱም አሁን በምንኖርበት ሕይወት በመንፈስ ዳግም መወለድን፣ በመጪውም ዘመን አካላዊ ትንሣኤን አስገኝቶልናል፡፡ ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር የመተባበራችን ነገር በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ቁጥር 21 እና 22፣ በፊልጵስዩስ ምዕራፍ 3 ከቁጥር 10 እስከ 12 እና በቆላስያስ ምዕራፍ 2 ቁጥር 12 ውስጥም ትምህርቱ ተቀምጦልናል፡፡

ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር በመተባበራችን እውነታ ምክንያት፣ የእኛ ትንሣኤ የተረጋገጠ ሆኗል፡፡ እስኪ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ከቁር 20 እስከ 23 የተናገረውን አድምጡ፡፡

> አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል።
> ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና።
> ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን
> ይሆናሉና።
> ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው፥
> በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው፤ (1ኛ ቆሮ 15፥20-23)

በዚህ ስፍራ፣ ጳውሎስ የኢየሱስ ትንሣኤ የእርሱ የሆኑትን ሁሉ የሚያካትት በኩራት መሆኑን አመልክቷል፡፡

በብሉይ ኪዳን፣ እስራኤል የመከሯን በኩራት ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርጋ እንድታቀርብ አዝዟል፡፡ ይህንንም በዘሌዋውያን ምእራፍ 23 ቁጥር 17 ላይ እንመለከታለን፡፡ እነዚህ የመከሩ በኩራት ፍሬዎች የአጠቃላዩ መከር ክፍሎች ናቸው ዋናውንም መከር ይወክላሉ፡፡ አቀራረባቸውም የአስተማማኝ ዋስትና ዓይነት ነው፡፡ ማለትም የመከሩን የመጀመሪያ በኩር ለጌታ ሲቀርቡ፣ እነርሱም በፊንታቸው መላውን መከር እንደሚሰበስቡ እምነታቸው መሆኑን እስራኤላውያን መግለጣቸው ነው፡፡ ኢየሱስንም ከሙታን በማስነሣት፣ እግዚአብሔር በተመሳሳይ መንገድ እኛንም እንደሚያስነሳን ያለውን ዕቅድ ገልጧል፡፡ እንግዲያው፣ እንደ አማኞች፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ ትንሣኤ አማካይነት የእኛንም የወደፊት አካላዊ ትንሣኤ ያተመው መሆኑን በማወቅ ስለ መነሣታችን ሙሉ መተማመን ሊኖረን ይገባል፡፡

ስለ አካላዊ ትንሣኤ ባደረግነው ጥናታችን፣ ለአካላዊ ሞት የዳረገንን እርግማን ደግሞም ለአካላችን ሕይወትን ያጎናፀፈውን ወንጌልን ተመልክተናል፡፡ አሁን በዚህ ነጥብ ላይ ደግሞ፣ አካላችን በእርግጥ የሚቤዥ መሆኑን ለመመልከት እንዘጋጃለን፡፡

# መቤዠት

የአካላችንን መቤዠት በሦስት ደረጃዎች እንመለከተዋለን፡ በመጀመሪያ፣ በዚህ በምድር ሕይወታችን ክርስቲያኖች የምንለማመደውን እናያለን፡፡ ሁለተኛ፣ በአካላዊ ሞት የሚጀምረውን የአካላችንን መካከለኛ ዘመን ሁኔታ እንዳስሳለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ በክርስቶስ መመለስ ወቅት በትንሣኤ የምናገኘውን አዲስ ሕይወት እንመለከታለን፡፡ ከአሁኑ ሕይወታችን እንጀምር፡፡

## አሁን የምንኖርበት ሕይወት

ምንም እንኳን ክርስቲያኖች በተለመደ መንገድ የአካላችንን መቤዠት በመጨረሻው ቀን ከሚሆነው ትንሣኤ አንፃር ቢነጋገሩበትም፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን የአካላችን መዳን የሚጀምረው መጀመሪያ ወደ እምነት በመጣንበትና መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ባደረበት ወቅት እንደሆነ ያስተምረናል፡፡ ይህም የመንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ማደር፣ በሮሜ ምዕራፍ 8 ከቁጥር 9 እስከ 11 ውስጥ ተገልጧል፡፡ ጳውሎስ በኤፌሶን ምዕራፍ 1 ቁጥር 13 እና 14 ላይ እንዳስተማረው ምንም እንኳን ወዲያውኑ አካላዊ ትንሣኤን ባንቀበልም፣ ወደፊት የሚሆነው አካላዊ መቤዠታችን እውን መሆኑን በአስተማማኝ ማኅተም አትሞልናል፡፡

መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን የማደሩን በረከትም አካላችን በዘመኑ ሁሉ ማጣጣሙን ይቀጥላል፣ ይህም በተለይ በቅድስና ሂደት ውስጥ የበለጠ እውን ይሆናል፡፡ አካላዊ መቀደሳችን ከነፍሳችን መቀደስ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ለእግዚአብሔር ይለየናል ያነፃናልም፡፡ በሕይወት ዘመናችንም ሁሉ በአካላችን የምንሠራውን ኃጢአት ይቅር እያለን እና አካላችንንም ጌታን ቢሚያከብር መንገድ እያዘጋጀ የመቀደሱን ሥራ ይቀጥላል፡፡ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 20 እንዳስተማረውም እግዚአብሔርን በሰውነታችን እንድናከብር ያስችለናል፣ ደግሞም በሮሜ ምዕራፍ 12 ቁጥር 1 ላይ እንደምናነብበው ሰውነታችንን ለእግዚአብሔር ሕያው መስዋዕት አድርገን እንድናቀርብም ያስችለናል፡፡

# የመካከለኛው ዘመን ሁኔታ

አማኞች አሁን በሚኖሩበት ሕይወት ከተጀመረው የአካላችን መቤዠት በኋላ፣ በአካላዊ ሞታችንም ወቅት ሂደቱ ይቀጥላል፡፡

ስንሞት፣ አካላችን ከነፍሳችን ለጊዜው ይለያል፡፡ ይህ እርከን በተደጋጋሚ የመካከለኛው ዘመን ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህም ዘመን አሁን በሚኖረን የምድር ሕይወትና በትንሣኤ በምናገኘው ሕይወት መካከል ያለው ጊዜ ነው፡፡ በዚህ መካከለኛ ዘመን ነፍሳችን ከክርስቶስ ጋር በመንግሥተ ሰማይ ትቆያለች፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለዚህ ጉዳይ እንደ ማቴዎስ ምዕራፍ 17 ቁጥር 3 እና 2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 6 እስከ 8 በመሳሰሉ ስፍራዎች ላይ ይናገራሉ፡፡

ነፍሶቻችን በመንግሥተ ሰማያት ሲቆዩ፣ አካሎቻችን ግን በምድር ይቆያሉ፡፡ ሰውነታችን አሁንም በኃጢአት የረከሰ ነው፣ ይህም በስባሽ በመሆናቸው እውነታ የተረጋገጠ ነው፡፡ ግን ያረከሳቸው ኃጢአት ከሞት በኋላ ኃጢአትን እንድንሠራ ተፅዕኖ ሊያሳድርብን አይችልም፡፡ ጳውሎስ በሮሜ ምእራፍ 6 ከቁር 2 እስከ 11 እንዳስተማረው፣ በአንድ በኩል፣ ሞት ከኃጢአት ገዢነት ነፃ ያወጣናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ፣ አካሎቻችን በመቃብር ውስጥ ምውት ሆነው፣ በጎም ይሁን መልካም የትኛውንም ሃሳብ ማሰብ የማይችሉ፣ የትኛውንም ተግባር መፈፀም የማይችሉና ስሜት አልባ ሆነው ይጋደማሉ፡፡

ምንም እንኳን አካሎቻችንና ነፍሶቻችን ለጊዜው በሞት ቢለዩንም፣ አካሎቻችን የእኛ ክፋይ መሆናቸው ግን ጨርሶውኑ አይቀርም፡፡ ይቀበሩም፣ ይቃጠሉም ወይንም የጠፉ ይምሰሉም፣ አካሎቻችን የእኛ ክፋይ ሆነው ይቀጥላሉ፡፡ ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑ በደርዘን ሊሰፈሩ የሚችሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክፍሎች አሉ፡፡ ለአብነት ያህል፣ 1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 25 ቁጥር 1 ሳሙኤል በገዛ ቤቱ በአርማቴ ተቀበረ ይላል፡፡ 1ኛ ነገሥት ምዕራፍ 2 ቁጥር 10 ደግሞ ዳዊት በዳዊት ከተማ በኢየሩሳሌም ተቀበረ ይላል፡፡ በ1ኛ እና በ2ኛ ነገሥት እንዲሁም በሁለተኛ ዜናም

ጭምር፣ የይሁዳ ነገሥታት በመደበኛነት በአባታቸው በዳዊት ከተማ እንደተቀበሩ እንመለከታለን፡፡ አካሎቻቸው አሁንም የእነርሱ ናቸው፣ አሁንም የስብዕናቸው ክፋዮች ናቸው፡፡

የዌስት ሚኒስተሩ አጭር ካቴኪዝም ሞታችንን በጥያቄና መልስ በዚህ መንገድ ያቀርበዋል፡፡

ጥያቄው፡

*አማኞች በሞት ወቅት ከኢየሱስ የሚያገኙት ጥቅም ምንድን ነው?*

ምላሹ፡

*የአማኞች ነፍስ በሞታቸው ወቅት ትቀደሳለች፣ ወዲያውኑም ወደ ክብር ትለወጣለች፤ አካሎቻቸውም፣ ከክርስቶስ ጋር ይተባበራሉ፣ እስከ ትንሣኤ ዕለትም፣ በመቃብር ውስጥ ያርፋሉ፡፡*

በዚህ ስፍራ፣ ካቴኪዝሙ እንደሚናገረው አማኞች በሞታቸው ወቅት የሚጠብቃቸው እጣፈንታ ሁለት ነው፡፡ አንዱ ለነፍሳቸው ሲሆን፣ አንዱ ደግሞ ለአካሎቻቸው ነው፡፡ ነፍሶቻችን ወደ መንግሥተ ሰማይ በክብር ይሸጋገራሉ፣ አካሎቻችን ግን ከክርስቶስ ጋር በመተባበር፣ በመቃብሮቻቸው ያርፋሉ፡፡ በዚያም በታላቅ ዝምታ ውስጥ ሆነው፣ በትንሣኤ የሚያገኙትን አዲስ ሕይወት ይጠባበቃሉ፡፡

*ነፍሳችን በመንግሥተ ሰማይ አካላችን ደግሞ በመቃብር ሲሆኑ፣ በአንድ ጊዜ በሁለት የተለያዩ ስፍራዎች መገኘታችንን መናገር እውነትነት አለው፡፡ ይህም ማብራሪያ የሚፈልግ ነገር ነው፣ በአጭሩ ካቴኪዝም ላይ የተሰጠው ምላሽ ለዚህ ነጥብ በጣም ጥሩ ነው፡፡ "የአማኞች ነፍስ በሞታቸው ወቅት ትቀደሳለች፣ ወዲያውኑም ወደ ክብር ትለወጣለች፤ አካሎቻቸውም፣ ከክርስቶስ ጋር ይተባበራሉ፣ እስከ ትንሣኤ ዕለትም፣ በመቃብር ውስጥ ያርፋሉ፡፡" ነፍስ ከሥጋ ስለመለየቷ የተጠቀሰው የመጀመሪያው ክፍል በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 1 እስከ 10 የተጠቀሰው ርዕሰ ጉዳይ አካል ነው፡፡ ጳውሎስ መዋቲ ምድራዊ አካሉን እንደ ምድራዊ ድንኳን ይገልጠዋል ኢ-ተፈጥሯዊ ነውና የሞትንም ትዕይንት ፈጽሞ አይወደውም ምክንያቱም ነፍሱ ከአካሉ ተለይታ ትወጣለች፡፡ [ዶ/ር ኖክስ ቻምበሊን]*

ይህ በአንድ ጊዜ በሁለት ቦታ የመገኘት ውጥረት በመንግሥተ ሰማያት ውስጥ እንኳን ይሰማናል፡፡ መንግሥተ ሰማያት ከምንገምተው በላይ አስደናቂ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም፡፡ ግን አካላችን ገና የትንሣኤ አካሉን አልለበሰምና በመንግሥተ ሰማያትም ውስጥ እንኳን በዚህ

ወቅት ድነታችን ገና ምሉዕ አይሆንም፡፡ እስኪ ጳውሎስ ስለ *ሥጋ* ትንሣኤ በሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 23 ላይ የሚናገረውን አድምጡ፡፡

> እርሱም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የመንፈስ በኵራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውስጣችን እንቃትታለን። (ሮሜ 8፥23)

በዚህ ስፍራ፣ ጳውሎስ በዚህ ሕይወት የምንቃትት መሆኑን ተናግሯል ምክንያቱም ገና የትንሣኤ ሰውነታችንን አልተቀበልንምና ነው፡፡ ሆኖም በመንግሥተ ሰማያት የሚኖሩ ነፍሶች አዲሱን አካል ይጠባበቃሉ፡፡ እንግዲያው፣ በአንድ መልኩ እነርሱም የሚቃትቱ እንደሆነ እናስባለን፣ ምክንያቱም የአካሎቻቸውን መቤዠት ይጠባበቃሉና፡፡

> *አንዳንድ ሰዎች የምንለብሰው አካል ምቹ የምድር ልብሳችን ዓይነት ወይንም አማራጭ መፍትሄ እንደሆነና ፍፁም አካል አልባ መሆንን የምንናፍቅ እንደምንሆን አድርገው ያስባሉ፡፡ ይህም አስተሳሰብ ከመጽሐፍ ቅዱሱ እውነት ይልቅ እጅግ የሚወደድ ዓይነት ይመስላል፡፡ እንግዲያው፣ በአካላዊ ሞታችንና በተሰፋ በምንጠብቀው አካላዊ ትንሣኤ መካከል ባለው ሕይወት ውስጥ መሆን ምን መልክ ያለው ይመስላችኋል? ስለዚያ ነገር ምንም ዓይነት ምስላዊ ሪፖርት አልተሰጠንም፡፡ ግልፅ ማብራሪያም አልተሰጠንም፡፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጡን ምላሾች ግን እጅግ አስተማማኝና እጅግም የላቀ ዝምድናን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ በእርግጥ ከጌታ ጋር እንሆናለን፡፡ [ዶ/ር ግሌን ስኮርጂ]*

አሁን የምንኖርበትን ሕይወትና አካላዊ ሞታችንን በልቡናችን ይዘን፣ አሁን ደግሞ በአዲሱ ሕይወት ውስጥ የአካሎቻችን መቤዠት እንዴት ፍፁም እንደሚሆን እንመለከታለን፡፡

## አዲስ ሕይወት

በአጠቃላይ ትንሣኤ ወቅት፣ መልሰን ሕያዋን ስንሆን ሰውነታችን አዲስ፣ እንከን አልባ ሕይወትን ይቀበላል፡፡ በዚያ ትንሣኤ ውስጥ፣ የኃጢአት ፍዳ ለመጨረሻና ለዘላለም ከእኛ ይወሰድልናል፡፡ ስለዚህም ነገር በሮሜ ምዕራፍ 8 ቁጥር 23፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምእራፍ 15 ከቁጥር 12 እስከ 57 እና ፊልጵስዩስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 11 ላይ እናነባለን፡፡ የነገረ መለኮት ሊቃውንቱ ይህንን የድነታችንን እርከን ደግመው ደጋግመው ከመከበር ጋር ያጣቅሱታል፣ ምክንያቱም ያን ጊዜ ወደ ከበረና ፍፁም ወደ ሆነ ሰብዓዊ ማንነት እንለወጣለንና፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ መከበራችን ብዙ

ዝርዝሮችን አይሰጡንም፡፡ ጳውሎስ ግን በ1ኛ ቆሮንቶስ ውስጥ አሁን ባለው አካላችንና በሚከብረው አካላችን መካከል ያለውን ንፅፅር በጨረፍታ ያሳየናል፡፡ እስኪ በ1ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 15 ከቁጥር 42 እስከ 44 የጻፈውን አድምጡ፡

> የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል፤
> በውርደት ይዘራል፥ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፥ በኃይል ይነሣል፤
> ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ
> መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ። (1ኛ ቆሮ 15፥42-44)

በአሁኑ አካላችንና በትንሣኤ በምንለብሰው አካላችን መካከል ስለሚኖረው ቀጣይነት ወይንም መለያየት ቁርጥ አድርገን እንዲህ ነው ማለት አንችልም፡፡ ልክ የክርስቶስ አካል በትንሣኤው ወቅት ለውጡ ውስጥ ለውስጥ እንደተካሄደ ሁሉ፣ የእኛም አካል እንደዚያው ይለወጣል፡፡ ይታደሳሉም ፍፁምም ይሆናሉ፡፡ የማይሞቱ፣ የከበሩ፣ ኃያልና መንፈሳዊ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ግን ሙሉ በሙሉ ሰብዓዊም ይሆናሉ፡፡ በስተመጨረሻም በትንሣኤ፣ እግዚአብሔር ስለ እኛ ለዘወትር ያቀደውን ዓይነት ሰዎች እንሆናለን፡፡

አካሎቻችን በኃጢአት ምክንያት ይሞታሉ፤ አካላዊ ሞት በውድቀት ወቅት ለተገለጠው የሰው ልጅ ክፋት እግዚአብሔር የሰጠው ፍርድ ነው፡፡ የምሥራቹ ግን አካላችን የሚታደስ መሆኑን ወንጌል ማወጁ ነው፡፡ ምሉዕ ስብዕናችንን ማለትም አካልና ነፍሳችንን ሊቤዥ ኢየሱስ እንደመጣ ይነግረናል፡፡ ይህም ለታላቅ ደስታና ፍንደቃ ምክንያት ይሆነናል፡፡ በአካላዊ ትንሣኤያችን፣ በስተመጨረሻው በሞት ላይ ድልን እናውጃለን፡፡ በአዲሲቷ ምድርና ሰማይም እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን በረከት ሁሉ እንወርሳለን፡፡ በፍፃሜውም የኢየሱስ ክርስቶስን ድል በዐይኖቻችን እናያለን፡፡

እስካሁን ድረስ ድነትን አስመልክቶ ባደረግነው ውይይት፣ ስለ ኃጢአት ይቅርታና ስለ ሥጋ ትንሣኤ የሚናገሩትን የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ አንቀፆች ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ፣ የመጨረሻውን ርዕሳችንን፡ የዘላለም ሕይወት የሚለውን እንመለከታለን፡፡

# 4. የዘላለም ሕይወት

የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫው ስለ ዘላለም ሕይወት የሚያነሳው በመጨረሻው የእምነት አንቀፅ ላይ ነው፡፡

*በዘላለም ሕይወት*

*አምናለሁ፡፡*

በዚህ ነጥብ ላይ፣ የሃይማኖት መግለጫው ደጋግሞ የዘላለም ሕይወት ተብሎ ስለሚጠራውና የሥጋን ትንሣኤ ተከትሎ ስለሚመጣው ሕይወት ይናገራል፡፡ የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝብ በስተመጨረሻው ፍፁም፣ የተባረከ፣ የማይበሰብስና የማያልፍ ሕይወት ብድራት ይቀበላሉ የሚለውን እምነት የሃይማኖት መግለጫው ያረጋግጣል፡፡

ምንም እንኳን ስለ ዘላለም ሕይወት ልንለው የምንችለው እጅግ በርካታ ነገር ቢኖረንም፣ በዚህ ትምህርት ግን፣ በሦስት ነገረ ጉዳዮች ላይ እናተኩራለን፡፡ አንደኛ፣ የዘላለምን ሕይወት ወቅት እናነሳለን፡፡ መቼ ይጀምራል? ሁለተኛ፣ የዘላለምን ሕይወት ድንቅ ትሩፋቶች እንነጋገርባቸዋለን፡፡ ከሌሎቹ ሕይወቶች የሚለየው እንዴት ነው? ሦስተኛ ደግሞ፣ ለዘላለም የምንኖርበትን አድራሻ እናነሳለን፡፡ እስኪ ስለ ዘላለም ሕይወት ወቅት በመነጋገር እንጀምር፡፡

## ወቅት

*የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው መቼ ነው? የዘላለም ሕይወት እንዲሆንልንና እንዲበዛልንም እንደመጣ ክርስቶስ ተናግሯል፡፡ በክርስቶስ መሆን፣ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን፣ እጅግ የተመረጠውን የኑሮ ዘይቤ እንደሚያስተዋውቀን በእርግጠኝነት ነግሮናል፣ ያ ማለት ግን የዘላለም ሕይወት ነውን? የዘላለም ሕይወት የሚጀምረው ከዚህ መዋቲ ህላዌ ተላቅቀን ከዚያ ባሻገር ወዳለው ሕይወት ስንሻገር ነውን? የዘላለም ሕይወትስ የሚጀምረው በዚያን ወቅት ነውን? እርግጥ በአንድ በኩል መልሱ አዎን ነው፡፡ ሆኖም ግን ሌላ ገፅታ ደግሞ አለው፤ ያም አዲሱ ሕይወት፣ የክርስቶስ የትንሣኤ ሕይወት በመቃብር በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ምንኖርበት ማብቂያ ወደሌለው ዘላለም የምንሸጋገርበት ሕይወት ሲሆን እርሱም በእኛ ውስጥ ዘሩ የተዘራው ሕይወት ነው፡፡ እንግዲያው የማያልፈው ሕይወት የሚጀምረው አሁን ነው፣ እናም ይህ የዘላለም ሕይወት ማብቂያ የሌለው ጊዜ የሚቆይ ሕይወት ብቻ ብለን የምንገልጠው አይደለም ነገር ግን ይህ ሕይወት አሁን*

*ክርስቶስን እና እግዚአብሔርን ያማከለ ከዚያም ለሰው ዘር ሁሉ አስቀድሞ ወደተዘጋጀው ሕይወት ሙሉ በሙሉ ታድሰን የምንገባበት ምርጥ ሕይወት ነው፡፡ ምንም እንኳን ስቃይ በሞላባት፣ አታጋይ በሆነችና በወደቀች ዓለም ውስጥ ብንኖርም አሁንም በዚያ ሕይወት ውስጥ በመሳተፍ ላይ ነን፡፡ [ዶ/ር ግሌን ስኮርጂ]*

አማኞች የዘላለምን ሕይወት እንደ አሁን እውነታ የተቀበሉት መሆኑን ቅዱሳት መጻሕፍት ደጋግመው ይገልፃሉ፡፡ ይህንንም በዮሐንስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 28፣ በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 12፣ በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ከቁር 11 እስከ 13 እና በሌሎችም በርካታ ስፍራዎች ውስጥ እንመለከተዋለን፡፡ ከነዚህ መካከል አንዱን ለምሳሌ ለማንሳት ያህል፣ በዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 24 ላይ ኢየሱስ የተናገረውን አድምጡ፡

እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም። (ዮሐ 5፥24)

ኢየሱስና የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት አንዳንድ ጊዜ ስለ ዘላለም ወይንም ስለ ዘላለም ሕይወት ሲናገሩ ከክርስቶስ ጋር ካለን ኅብረት የሚገኝ የአሁን ዘመን እውነታ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ይህም በመሠረቱ እውነት ነው፡፡ አካላችን መዋቲ ቢሆንም፣ ነፍሳችን ግን አትሞትም፡፡ አሁን ያለን መንፈሳዊ ሕይወት ለዘላለም ከሚኖረን ሕይወት ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ በመጨረሻው ፍርድ ቀን የዘላለምን ሕይወት ውርሳችን አድርጎ እንደሚሰጠን ቅዱሳት መጻሕፍት በበለጠ መንገድ ደጋግመው ይናገራሉ፡፡ ይህንንም ማቴዎስ ምዕራፍ 25 ቁጥር 46፣ ማርቆስ ምዕራፍ 10 ቁጥር 29 እና 30 እና ይሁዳ ቁጥር 21 በመሳሰሉት ክፍሎች ውስጥ እንመለከተዋለን፡፡ አንዱን ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፣ ዮሐንስ በወንጌሉ ምዕራፍ 6 ቁጥር 40 ላይ የጻፈውን አድምጡ፡፡

ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ። (ዮሐ 6፥40)

ዮሐንስ በዚህ ስፍራ እንዳደረገው ሁሉ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትም በተደጋጋሚ የዘላለምን ሕይወት በሙላት የመቀበላችንን ነገር ከአካላዊ ትንሣኤያችን ጋር ያዛምዱታል፡፡ አካላችን ሕያው ሲሆን፣ አካልና ነፍስ ኖሮን፣ ፍፁም የተዋጀን እና የታደሰን ሰብዓዊ ፍጡራን ሆነን ለዘላለም እንኖራለን፡፡

*ከክርስቶስ ጋር ካለን ኅብረት የተነሳ፣ በክርስቶስ ያገኘነው ነገር፣ ያም “አሁን ያለን” እና “ገና ያልተቀበልነው” ምን እንደሆነ ማብራራቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ይህንንም ስል ማለት የፈለግሁት፣ ክርስቶስን ስንቀበል፣ በክርስቶስ ላይ እምነታችንን ባደረግንበት ወቅት የእኛ የሆነውን “የተቀበልነውን” የዘላለምን ሕይወት ጨምሮ በክርስቶስ የመሆንን ትሩፋት ሁሉ ማለቴ*

*ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ የእኛ ናቸው፤ የዘላለምም ሕይወት ተቀብለናል፡፡ ሆኖም ደግሞ፣ "ገናም ያልተቀበልነው" አለ፡፡ በዚህም ረገድ ማለት የፈለግነው ክርስቶስን ከተቀበልን በኋላ እንኳን አብዛኞቻችን እናረጃለን፣ ብዙዎቻችንም እንታመማለን፣ ክርስቶስም ዳግመኛ እስካልተመለሰ ድረስ አብዛኞቻችንም እንሞታለን ነው፡፡ ስለዚህም "ገና ያልተቀበልነው" አሁንም ለእኛ ተጠብቆልናል፡፡ እንግዲያው "የተቀበልነውና" እና "ገና ያልተቀበልነው" ከሚለው ሃሳብ የምንረዳው፣ አዎን የዘላለም ሕይወት አግኝተናል፣ በተመሳሳይ ሁኔታም የዘላለም ሕይወት በአዲሲቷ ሰማይና ምድር ውስጥ ለእኛ ተጠብቆልናል የሚለውን ነው፡፡ [ዶ/ር ጄፈሪ ጁ]*

ለነፍሳችን የሆነው የዘላለም ሕይወት ዳግም በተወለድንበት ወቅት ጀምሯል ብሎ መናገር አግባብነት ያለው መሆኑን የምንገነዘብበት ሁኔታ አለ፡፡ ሆኖም በመጨረሻው ፍርድ አካላዊ ትንሣኤን እስከምናገኝበት ቀን ድረስ ግን ሙሉ በሙሉ ሕያዋን አንሆንም፡፡ ያን ጊዜ ብቻ በሁለንተናችን በእግዚአብሔር ፊት ሕያዋን እንሆናለን፡፡ ከዚያን በፊት ግን፣ በነፍሳችን መቤዠት በኩል የዘላለምን ሕይወት ቅምሻ እናጣጥማለን፡፡ አካሎቻችንም አዲስን ሕይወት ሲቀበሉ ግን እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀውን ኑሮ እንኖራለን፡፡

የዘላለምን ሕይወት ወቅት ግንዛቤ በዚህ መልክ ከጨበጥን፣ አሁን ደግሞ ስለ ድንቅ ትሩፋቶቹ እንመልከት፡፡

## ድንቅ ትሩፋቶች/መለያዎች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ የዘላለም ሕይወት ማለት የእኛ ኑባሬና ሕሊና ለዘላለም ይቀጥላል የማለት ጉዳይ ብቻ አይደለም፡፡ በዘላለም ፍርድ ውስጥ ያሉትም ሰዎች አንኳን በነዋሪነታቸውና በነቃ ኅሊናቸው ይዘልቃሉ፡፡ የዘላለም ሕይወት ወሳኝ ድንቅ ትሩፋት/መለያ ግን በእግዚአብሔር በረከት ውስጥ ለዘላለም መኖራችን ነው፡፡ በዚህ ረገድ፣ ሕይወት ማግኘት ማለት የእግዚአብሔርን ሞገስና በረከት መቀበል ማለት ነው፡፡ በተቃራኒው ደግሞ፣ በሞት መቀጣት ማለት ደግሞ በእርሱ ቁጣና እርግማን ስር መውደቅ ማለት ነው፡፡ የዘላለም ሕይወትም ሆነ የዘላለም ሞት ሁለቱም ዘላለማዊ ኑባሬ ናቸው፡፡ በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የኑባሬው ምንነት ነው፡፡ ልክ ኢየሱስ በዮሐንስ ምዕራፍ 17 ቁጥር 3 ላይ እንደፀለየው ማለት ነው፡

> እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት። (ዮሐ 17፥3)

በዚህ ስፍራ፣ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ማለት እግዚአብሔርንና ኢየሱስ ክርስቶስን ከማወቅ ጋር አቻ መሆኑን አስተምሯል፡፡ በዚህ አውድ፣ ማወቅ የሚለው ሃሳብ የሚያመለክተው በፍቅር ላይ የተመሠረተን ግንኙነት ነው፡፡ ኢየሱስ ያነሳው ነጥብ የዘላለም ሕይወት እንዲያው በሕሊና

ንቁ ሆኖ መኖር ብቻ ተደርጎ ሊፈታ የማይገባ መሆኑንና በፈንታው ግን የእግዚአብሔርን ፍቅር ማጣጣም መሆኑን ነው፡፡

ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 7 ከቁጥር 9 እስከ 11 ስለ ሕይወትና ሞት የተናገረውን እስኪ እንመልከት፡

> እኔም ዱሮ ያለ ሕግ ሕያው ነበርሁ፤ ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኃጢአት
> ሕያው ሆነ እኔም ሞትሁ፤
> ለሕይወትም የተሰጠችውን ትእዛዝ እርስዋን ለሞት ሆና አገኘኋት፤
> ኃጢአት ምክንያት አግኝቶ በትእዛዝ አታሎኛልና በእርስዋም ገድሎኛል።
> (ሮሜ 7፥9-11)

ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የገለጠው በዘመኑ ሁሉ በአካልም በአዕምሮም ህያው ነበርሁ በማለት ነው፡፡ በጎሊና ንቁና አስተዋይ ማንነት ያለው ሆኖ ይኖር ነበር፡፡ ሆኖም ደግሞ፣ መጀመሪያ ሕያው ነበርሁ፣ በኋላ ሞትሁ፣ ለሞት አልፌ ተሰጠሁ ይላል፡፡ ልዩነቱ በእግዚአብሔር ፊት መቆሙ ነው፡፡ ሕግ ሳይፈርድበት በፊት፣ ሕያው ነበር፡፡ ሕግ በእርግማን ስር ሲያኖረው ግን፣ ጳውሎስ ሞተ፡፡ ኋላ ደግሞ፣ ወደ ክርስቶስ ሲመጣና እርግማኑ ሲወሰድለት፣ አዲስ ሕይወት ያገኘ ሰው ተብሎ ተገለጠ፡፡ ይህንኑ ተመሳሳይ ሃሳብ በዮሐንስ ምዕራፍ 5 ቁጥር 24 እና በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 14 ላይ እንመለከታለን፡፡

እስኪ ስለዚህ ነገር በዚህ መንገድ አስቡ፡ በመጨረሻው ቀን፣ በአጠቃላይ ትንሣኤ ሙታን ሁሉ ይነሣሉ፡፡ የማትሞተው ነፍሳችን ከትሣኤ አካላችን ጋር ትዋሃዳለች፡፡ እንደ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ከቁጥር 28 እስከ 29 አገላለጥ፣ በጎ ያደረጉ ሁሉ ለሽልማት ይነሣሉ፣ ክፉ ያደረጉ ደግሞ ለፍርድ ይነሣሉ፡፡ ሁለቱም በትንሣኤ አካላቸው ለዘላለም በሕያውነት ይኖራሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የጻድቃንን ዕጣፈንታ "ሕይወት" ሲለው፣ የከፉዎችን ደግሞ "ሞት" ይለዋል፡፡ ልዩነቱ የመኖራቸውና ያለመኖራቸው ወይንም ያለማሰባቸው ወይም የልምምዳቸው ጉዳይ አይደለም፡፡ ልዩነቱ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ነው፡፡ በእግዚአብሔር በረከት ስር ከኖርን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ሕያዋን ናችሁ ይለናል፡፡ በእርግማን ስር ከሆንን ግን፣ ሙታን ናችሁ ይለናል፡፡ ስለዚህ፣ የዘላለም ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር በማይቋረጥ የተባረከ ግንኙነት ሕያው ሆኖ መኖር ነው፡፡ ግን እነዚህ በረከቶች ምንድን ናቸው? የተባረከስ ሕይወት ምን ይመስላል?

*ከእግዚአብሔር ጋር የምንኖረውን የዘላለም ሕይወት በደመና ላይ የመንሳፈፍ ዓይነት አድርገን ልንስለው አይገባም ብዬ አስባለሁ፡፡ ነገር ግን፣ ኃጢአት፣ ህመምና ሞት ድርሽ የማይልባቸው የትንሣኤ አካላትን እንለብሳለን፡፡ የማንበሰብስም እንሆናለን፣ ሞትም አይነካንም፡፡ በአዲስ ምድርም እንኖራለን፡፡ ዝርዝሮቹን ግን በውል ልንጨብጣቸው*

*አንችልም ስለዚህም ይህ ጉዳይ ምን ምንን ያካትታል? ዝርዝሩን አናውቅም፣ አንድ ሃላፊነት እንደሚኖረን ግን እናውቃለን፡፡ ከክርስቶስ ጋር እንነግሣለን፡፡ አዲስ ፍጥረተ-ዓለም እስከ ሆነ ድረስ፣ እግዚአብሔር ከፈጠረው ኅብረ-ከዋክብት ጋር አንድ ግንኙነት ይኖረናል ብዬ እወስዳለሁ፡፡ ስለዚህ እኛ የምናከናውናቸው አንዳንድ ውሱን ነገሮች ይኖራሉ፡፡ በመሠረታዊነት ግን፣ አዲስ ኪዳን ትኩረት እንደሰጠበት፣ በዚያ ቁም ነገሩ እኛ የምናከናውነው ነገር አይደለም፣ ግን እጅግ የሚማርክ፣ እጅግ የሚያስፈነድቅና የተሳካ ነገር ይሆናል፡፡ ያም አዲስ ኪዳን እንዳስቀመጠው እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ይሆናል፡፡ እኛም ፊት ለፊት እናየዋለን፡፡ ከእርሱ ጋር ኅብረት ማድረግ ማለቂያ የሌለው ሃሴትና ደስታችን ይሆናል፡፡ [ዶ/ር ቶም ሽሬይነር]*

ከ1873 እስከ 1957 (እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር) የኖሩት፣ እውቁ የነገረ-መለኮት ምሑር ሉዊስ በርክሆፍ፣ በሲስተማቲክ ቴዎሎጂ መጽሐፋቸው ክፍል 6 ምዕራፍ 5 ላይ ስለዘላለም ሕይወት የመጨረሻ እርከን እንዲህ የሚል መግለጫ ሰጥተዋል እስኪ አድምጡ፡

*ከእግዚአብሔር ጋር በአንድ ላይ ሆነው ሕይወትን በሙላት ያጣጥማሉ… እግዚአብሔርንና ኢየሱስ ክርስቶስንም ፊት ለፊት ያያሉ… በእርሱም እርካታን ያገኛሉ፣ በእርሱም ደስ ይላቸዋል ያከብሩታልም… እጅግ ከፍ ባለ እርከንም መከባበርና ማኅበረሰባዊ ግንኙነት ይኖራል… የእያንዳንዱም ሰው ሃሴትና ደስታ ፍፁምና ምሉዕ ይሆናል፡፡ [ሉዊስ በርክሆፍ]*

በአንዳንድ መንገዶች፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዘላለማዊ ሕይወት ተፈጥሮ ብዙም አለመናገሩ እንግዳ ይመስላል፡፡ ከሁሉ በላይ ግን፣ የዘላለም ሕይወት ንስሓ በመግባት በክርስቶስ የሚገኘውን የሚያድን እምነት ለተቀበሉ ሁሉ ወንጌል የሚሰጠው ትልቅ ብድራት ነው፡፡ እውነታው ግን ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ ዘላለም ሕይወት የሚናገሩት ጠቅለል ባለ ሁኔታ ብቻ መናገራቸው ነው፡፡ ራዕይ ምዕራፍ 21 ቁጥር 3 እና 4 እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል እንደሚኖርና ከዚያም ወዲያ ሞትና ኃዘን እንደማይኖር ይነግረናል፡፡ አዲስ አካል እንለብሳለን፣ አሁን በላያችን ከተጫነውም የኃጢአት እርኩሰትና ተፅዕኖም ነፃ እንወጣለን፡፡ ዝርዝር ጉዳዮቹስ? ብለን ብንጠይቅ እውነታው መጽሐፍ ቅዱስ በጣም ጥቂት ብቻ መናገሩ ነው፡፡ ይልቁኑ፣ በእግዚአብሔር መልካምነት እንድንታመን እና ለእኛ ምን አዘጋጅቶልን ይሆን በማለት በጣምም እንዳንዋተት ያሳስበናል፡፡ ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስምዕራፍ 12 ከቁጥር 2 እስከ 4 የጻፈውን አድምጡ፡

ሰውን በክርስቶስ አውቃለሁ፥ በሥጋ እንደ ሆነ አላውቅም ወይም ከሥጋ ውጭ እንደ ሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል፤ እንዲህ ያለው ሰው ከዐሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ። እንዲህ ያለውንም ሰው አውቃለሁ፥ በሥጋ እንደ ሆነ ወይም ያለ ሥጋ

እንደ ሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል፤
ወደ ገነት ተነጠቀ፥ ሰውም ሊናገር የማይገባውን የማይነገረውን ቃል
ሰማ። (2ቆሮ 12፥2-4)

ጳውሎስ ስለዚህ ልምምድ የተናገረውን ልብ በሉ፡፡ የተሰማው ነገር ሊገለጥ የማይችል ነው፣ በሰብዓዊ ቋንቋ በሚያረካ መንገድ ሊገለጡ አይችሉም፡፡ ከዚያም በላይ፣ ሰው ሦስተኛው ሰማይ ምን ምን እንደያዘ እንዲናገር አልተፈቀደለትም፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር ነገሩን አሁን በምሥጢር እንዲቆይ ማድረጉ እጅግ አስደናቂ ነው፡፡

ከትንሣኤ በፊት የምንቆይበት መካከለኛ ስፍራ መንግሥተ ሰማያት እንግዲህ ያ ነው፡፡ የመንግሥተ ሰማያት ነገር ምሥጢር ከሆነ ዘንድ፣ የመጨረሻችንማ ምን ያህል እጅግ ምሥጢራዊ ይሆን? ክርስቶስ ሲመለስ የሚኖረው ሕይወት ምንኛ አስደናቂ እንደሚሆን እንዴት መገመት ይቻላል? መጽሐፍ ቅዱስ ከእንግዲህ ወዲያ ሃዘን፣ መከራ፣ ተስፋ መቁረጥና ሞት አይኖርም በማለት ይነግረናል፡፡ ነገሮቹ አስደናቂና እውን ናቸው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለ እነርሱ ብዙ ዝርዝር አይሰጠንም፡፡

የዘላለምን ሕይወት ወቅትና መለያ ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ ወደ መጨረሻው ርዕሳችን፤ ለዘላለም ወደምንኖርበት ስፍራ መለስ ብለን እንመልከት፡፡

# ስፍራ/ቦታ

ቅዱሳት መጻሕፍት ለዘላለም የምንኖርበትን ስፍራ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር በማለት በተደጋጋሚ ይጠሩታል፡፡ ይህንንም አነጋገር በኢሳያስ ምዕራፍ 65 ቁጥር 17 እና ምዕራፍ 66 ቁጥር 22፣ በ2ኛ ጴጥሮስ ምዕራፍ 3 ቁጥር 13 እና በራእይ ምዕራፍ 21 ቁጥር 1 ላይ እናገኘዋለን፡፡ የአዲስ ሰማይና ምድር እንደገና መፈጠር የመጽሐፍ ቅዱስን ሁሉን ገዢ የታሪክ ፍሰት ወደ ሙላት ያመጣዋል፡፡ ታሪክ የሚጀምረው በዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ቁጥር 1 ላይ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በፈጠረበት ወቅት ነው፡፡ ከዚያን በኋላ ግን በሰው ልጅ በኃጢአት ውስጥ በመውደቁ ምክንያት ረከሰ፣ እግዚአብሔር ሊገለጥበት በወደደውም መጠን ሊገለጥበት የማይመጥን ሆነ፡፡ ከዚያን በኋላ የቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሁሉ የሚያወሳው የሰው ዘርና ፍጥረት ስለሚቤዥበት ታሪክ ነው፡፡ ኢየሱስም ዳግም ሲመለስ፣ የሚሆነው የመጨረሻ ውጤት ሰማይና ምድር ይቤዣሉ ይታደሳሉም፣ እግዚአብሔርም ትንሣኤ በሰጣቸው ህዝቡ መካከል ይኖራል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት ልንጸልይ እንደሚገባን ባስተማረበት በማቴዎስ ምዕራፍ 6 ቁጥር 9 እና 10 ላይ በልቡናው የነበረው ግብ ይኸው ነበር፡፡

እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ። በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፥ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤ (ማቴ 6፥9-10)

ግቡ የእግዚአብሔር መንግሥት በሰማያት፣ መላዕክትና ከምድር የተለዩ ቅዱሳን ነፍሶች በሚኖሩበት፣ ደግሞም በምድር፣ እኛ በምንኖርበት፣ በሙላት እንድትገለጥ ነበር፡፡ መንግሥቱ በምድር እንድትመጣ፣ ፈቃዱም ልክ በሰማያት እንደምትከበር ሁሉ በምድርም እንድትፈፀም እንድንለምን ኢየሱስ ያስተማረን ለዚህ ነበር፡፡

ቅዱሳት መጻሕፍት ስለ አዲሱ ፍጥረት ደጋግመው ባይናገሩም እንኳን፣ ሲፈፀም ግን የተቤዡት ሰዎች የመጨረሻ አድራሻቸው በሰማያት ብቻ ሳይሆን በአዲሲቱም ምድር መሆኑን ግልፅ ያደርጋሉ፡፡ ለአብነት ያህል፣ በኢሳያስ ምዕራፍ 65 ቁጥር 17 እስከ 19፣ የእግዚአብሔር ህዝብ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም እንደሚኖሩ እንረዳለን፡፡ በራዕይ ምዕራፍ 21 ቁጥር 2 ደግሞ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በአዲሷ ምድር እንደምትገኝ ግልፅ ያደርጋል፡፡ በራእይ ምዕራፍ 21 ከቁጥር 1 እስከ 5 ዮሐንስ የጻፈውን አድምጡ፡

አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም።
ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።
ታላቅም ድምፅ ከሰማይ። እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤
እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።
በዙፋንም የተቀመጠው። እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም። እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞች ናቸውና ጻፍ አለኝ።
(ራእይ 21፥1-5)

በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንዳዘጋጀ እንመለከታለን፡፡ አዲሲቷ ምድርም ተዘጋጅታ ስታልቅ፣ አዲሲቷን ኢየሩሳሌምን ያመጣና በህዝቡ መካከል የሚያድርባት ቅድስት ምድር ያደርጋታል፡፡ የእግዚአብሔር እቅዱ እኛን ወደ ሰማይ ወስዶ ለዘላለም ማኖር

ከሆነ፣ አዲስ ምድር አስፈላጊ አይሆንም ነበር፡፡ በዚህ ስፍራ እንደምናብበው ግን፣ እግዚአብሔር ሁሉን አዲስ ያደርጋል፣ ይህም እኛ የምንኖርበትን የዘላለም መኖሪያ ያካትታል፡፡

ከ354 እስከ 430 (እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር) የኖረው፣ ቀደምት የቤተክርስቲያን አባትና የሂፖው ጳጳስ አውጉስቲን፣ *The City of God* በተሰኘው ሃያኛው መጽሐፉ፣ ምዕራፍ 16 ላይ ስለ አዲሷ ምድር እንዲህ ጽፏል፡

*ዓለም ራሷ ወደ ተሻለ ነገር ስትለወጥ፣ ሰዎች ባሉበት ሁኔታ ቢኖሩባት መልሳ ትረክሳለች፣ ስለዚህ ሰውነታቸው ራሱ ወደ አንድ የተሻለ ነገር ሊለወጥ ይገባዋል፡፡ [አውጉስቲን]*

*እግዚአብሔር ሁሉን አዲስ የሚያደርግበት ቀን ይመጣል፡፡ ይህንን ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን፣ እኛንም ባስተማረበት ድንቅ ቃሎች ውስጥ እንመለከታለን፡ "በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ፣ ስምህ ይቀደስ፣ መንግሥትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፡፡" ወሳኙ፣ ማዕከላዊውና መሠረታዊው ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ አሁን የምንኖረው በሰማያት ያለው እውነታ የምድርም እውነታ የሚሆንበትን ጊዜ በመጠባበቅ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት እግዚአብሔር ሲቀደስ፣ ነገሮች ሁሉ ትክክል ሲሆኑ፣ ጽድቅ፣ ክብር፣ እውነት እና ፍቅር ይነግሣሉ ማለት ነው፡፡ እንደ ክርስቲያኖች የሚኖረን ተስፋ፣ እርግጠኛው ተስፋችን፣ አዲሱ ፍጥረት የእኛ የዘላለም መኖሪያ እንደሚሆን ቅዱሳት መጻሕፍት ያሰፈሩት ተስፋ መሆኑ ነው፡፡ [ዶ/ር ጆናታን ፔኒንግተን]*

አዲሲቷ ምድር የመጨረሻዋ መኖሪያችን የመሆኗ እውነታ ከተሰወረብን፣ ከነባራዊው ተጨባጭ እውነታ ራሳችንን ለመነጣጠል ቀላል ይሆናል፣ ስለዚህም አሁን በምድር የምንኖረው ሕይወት የበረከት መሆኑ ቀርቶ የመከራ ይሆንብናል፡፡ ነገር ግን አሁን ስላለንባት ምድር ያለን አመለካከት ሲቀየር፣ ከእግዚአብሔር የምንጠብቃትና የታደሰችው የዘላለም መኖሪያችን ውበትና በረከት ቅምሻ እንደሆነች እንገነዘባለን፡፡

# 5. ማጠቃለያ

በሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ላይ በተመሠረተው በዚህ ትምህርታችን፣ በድነት ርዕስ ላይ አተኩረናል፡፡ በኃጢአት ምክንያት ከመጣብን ጣጣ ይቅርታን ስለመቀበላችን፣ ስለ መለኮታዊ ጸጋ፣ እና ስለ ሰው ሃላፊነት ተነጋግረናል፡፡ ስለ ሥጋ ትንሣኤ ደግሞ ስለ ሞት እርግማን፣ ስለ ሕይወት ወንጌልና በክርስቶስ ስለተገኘው ቤዛነት ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የዘላለምን ሕይወት ወቅት፣መለያና ስፍራም ለመዳሰስ ሞክረናል፡፡

በዚህ የድነት ትምህርታችን ውስጥ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫ ያተኮረባቸውንና ቤተክርስቲያንም ለሺህ ዓመታት አፅንታ የያዘቻቸውን የተለመዱ ክርስቲያናዊ የእምነት መግለጫዎች ተመልክተናል፡፡ እነዚህን መደበኛ አስተምህሮዎች በልቡናችን ከያዝን በሌሎች ቤተ እምነቶችና ልምምዶች ውስጥ ካሉ ክርስቲያኖች ጋር በምንነጋገርበት ጊዜ ሁሉ፣ የሐዋርያት የሃይማኖት መግለጫን ከሚቀበሉት ጋር አንድነትን ልንመሠርት የምንችልባቸው ጠንካራ መሠረቶች ሲኖሩን ከዚያ የሚያፈነግጡትንም ለማረም የምንችልበት አቅም ይኖረናል፡፡ ከዚያም ባሻገር፣ በነዚህ መሠረታዊ የትምህርተ ድነት ነጥቦች ላይ ስናተኩር፣ እግዚአብሔር በዚህ ምድር እያከናወነ ያለውን ትልቅ ምስል እንጨብጣለን፣ በዚህም ስለ ፍቅሩና ስለ ጸጋውም እርሱን የምናመሰግንባቸውን በርካታ ምክንያቶች እናገኛለን፡፡